# ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም

ከሄኖክ የሺጥላ

ስነ ግጥም

**የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው**

**Copyright© 2012**

## ማነኝ?

ማንም ነኝ (በይበልጥ ዘንደሮ፣ ኢትዮጵያዊነት ፅኑ ሮሮ በሆነበት ዘመን)። ግን ስለ አስተዳደገኔና ማንነቴ ማወቅ ለሚሻ አንባቢ ይህንን እላለሁ። የትኛውን ኮኮብ ቆጣሪ እንደሚጠራብ'ና ባላውቅም ለወላጆቼ ማደጐ ካልሆነኩኝ በ'ቀር ወይም ካልተሳሳቱ፣ የሰማዕቱ 'ስጢፋኖስ 'ለት የተያዘ ምጥ ከሶስት ቀን የ "ግፊው፣ አይዞሽ፣ በርቺ"ትግል በኹዋላ እናቴን ማሪያም ምራት የሃምሌ ገብርኤል 'ለት (ሲያውም ሲነግስ) እንደተወለደኩ ነግረውኛል። ለነገሩማ የከርስትና ስሜን ካልተናገርኩ ጣዩስ፣ቡዳውስ፣ሰላቢውስ፣ጠንቋዩስ፣ጥላ-ወጊውስ፣ደብተራወስ፣ሳህን ላይ ተህሊል ጣፊወስ፣ ህርዝ ሰፊውስ ምን ቸሎ? አረ ወዲያ!

አባቴ ሲታናናሽ ወንድሞቼ ስም ሲያወጣ የምጥ ሳአታቸው የጠፈ 'ለት መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጥ ያገኘውን ስም ይሰጣቸው እንደነበር ነግሮኛል፣ ታዲያ የኔም ስም መጽሓፈ ሄኖክን ሲያነብ "ቃለ-በረከት ዘ-ሄኖክ ዘከመ ባረከ ሕሩያን ወጻድቅ" በሚለው ቃለ ተመሰጦ ይሁን፣ ኢትዮጵያ የቃለ እግዚአብሔሩ መገኛ ምድር መሆኑዋን ለመዘከር የሁን፣ ወይም የሰለጠንኩና ትጉህ እንድሆንለት ፈልጎ ይሁን እስከ ዛሬ ድረስ እንቅጩን ምክንያት አልነገረኝም።እንደው ሳስበው እኛ ልጆቹ ሞት ሳናይ እንድንኖር ካለው ስር የሰደደ ምኞት የመነጨ ሊሆን ይችላል በዬም አሰባለሁ፣ ለዚህም ምስክሬ ሌላው ወንድሜን ኤልያስ ብሎ መጥራቱ ነው። ያም ሆኖ እንደ ቻይናዎች ከከፍታ ላይ ብርጭቆ ጥሎ ከሰብርባሪውና መሰበሩ ከፈጠረው ድምጽ ጋ የተቀናጀ ስም ሊሰጠኝ ባለመሻቱ አመሰግነዋለው። ደሞስ "ደም መላሽ" ብሎ ቢጠራኝስ ይችል ነበረ እኮ-እግዜር ሲያወጣኝ ደርግ ሊወድቅ ሲል ብቻም ሳሆን በወያኔ ዘመን ለጥቂት ከመወለድ ተርፌም እንጂ- አልያማ ያ ስም በርግጠኝነት የኔ መጠሪያ ይሆን ነበር። የምን ሄኖክ ሃገር ደም በደም እየሆንች? እኔም የማንን ደም እንደምመልስ፣ ከመለስኩም በሁዋላ ስሜ ደም መላሽ ሆኖ መቀጠሉ፣ ምናልባት አሸባሪ ስም ተብሎ... አረ ተዉት።

ጉልበቴ ታፈር ሲነሳ ምንተ ሃፍረቴን ( "በዚያን ግዜ ሹሹዬን") በፊደል ሸፍኜ ያሲቃ ማርዬን የቄስ ትምህርት እንድማር ተላኩ። የኔታ ማርዬን የሰማይ የምድሩ ጌታ ብድሩን ደርቦ ይክፈልልኝና ገና በመጀመሪያው ቀን ስስ ገላዬን ባ'ለንጋ ስለላጡት ታሊቃ ማርዬ ዘንድ ወጥቼ ተራራው ላይ ጉብ ካለውና የየኔታ ማርዬን የቄስ-ተማሪ ቤት ቁልቁል ማየት ከሚያስችለው ያሊቃ ዘነበ ተማሪ ቤት (አፈሩም ዛሬ ምድሪቷ ላይ የቆሙት ሃጥአኖችም ይቅለሉዋቸውና) ፊደል ቆጠርኩ። በህይወቴ ለመጀመሪያ ምናልባትም ለምጨረሻ ጊዜ እየገባኝ ተማርኩ። እነግዲህ ተ-አበገደ የሚዘል እውቀት የሌው ሰው ነኝ ማለት ነው። እሰይ እንኩዋንም ሌላው ሌላው አልገባኝ። ቢገባኝማ ኖሮ በማያገባኝ ና በማይገባኝ ነገር ተጠምጄ... አረ ተዉት። ይልቁንም የፊደል ቋቴ ሲፈታ በዚያን ጊዜ ፋኖስና ብርጭቆን በቃሉ ያነበንብ የነበረው ልጅ ዛሬ በራሱ ኩራዝ ብቅ አለ። ደስ ስል!!! ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር ብዬ፣ ብርሃን ይሁንንም አከዬበት መንገድ መዝጋቱን ገትቼ አንባቢ. ወደ-ዋናው ቁም ነገር ይገሰግስ ዘንድ እንሆ!!!

ሄኖክ የሺጥላ

# መታሰቢያ

ለባለቅኔው አባት አለም ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ፣ በ ምርጫ ፺፯ ወቅት በግፍ በግፈኞች ለተገደሉት የነጻ-ስርዓት ናፋቂ የኢትዮጵያ ልጆች፣ ለካፒቴን ተሾመ ተንኮሉ እናት ለወይዘሮ ሙሉ ጃኖ መታሰቢያ ይሁን። ይህች ጽሁፍ ከመቃብራችሁ ግርጌ የበቀለች ወይራ ብትሆንስ?

በመጨረሻም በመታሰቢያነት ብቻ ለማላልፈው የበረሃ ወንድሜ ስለሺ መኩተ፣ ዛሬ ካለህበት የወያኔ እስር የሚያስፈታህ ትናንት ያመንንበት ትግል ብቻ በመሆኑ፣ ታስረሕም መቀጠሉን፣ ቢገሉህም እንደማይቆም ጠንቅቀህ እንደምታውቅ ባውቅም፣ ከዚያ ካለህበት ጨለማ ክፍል ውስጥ ብቻህን እንዳልተዘጋብህ ታውቅ ዘንድ--እኒህ ፊደሎች ጉም የለበሱ እስቲመስለኝ ድረስ፣ እንባ ቢያስጠላኝም...ጨው በተሞሉ አይኖቼና ሳግ ባበደነው አንደበት "እውነት ያሸንፋል" ስልህ፣ በተማማልነው ቃላችን ውስጥ ዛሬም ቅንጣት ታህል ማፈግፈግ እናድልነባብን አውቃለሁ:

:አዋ-እውነት ያሸንፋል!!!

# ማውጫ


የ'ኔ አባት እሱ ነው....................1
ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም....................4
ፊቱ ሽራ ሆና ትዝታን የሚስል....................13
ንገሩን መቼ ንናደድ....................20
ገበሬው ምን ነካው....................24
አንቺ ሀገር....................35
መለከተ እምቢልታ ያበው እምቢልታ....................38
ፃፍ....................41
ይህንን ለማየት ነበር....................47
ወንድ ማለት....................53
የዘንድሮ ውስጠ ወይራ....................56
የት ሊደርስ ዛሬ ሃቅ ቢቀለበስ....................59
የመከራ ዘፋን....................66
ተረት ተረት....................70
የኔ ጥያቄ ይህን ነው....................75
በቅሎ....................82
ሰዩመ እግዚአብሄር....................88
ምን ትል ነበር....................95
አንገቱ ተጣሞ ቁምጣ ተሸከሞ....................99
እሱን ስመለከት ግጥሜ ተቋረጠ....................101
ንገረኝ እንግዲህ....................107
ግን ለምን ነው የምወድሽ....................112
ወገቧን ያማታል....................115

# መግቢያ

"ኪነ-ጥበብ 'ንጥር የህይወት ቅመም ነው" ይላል ባለቅኔው ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን። እውነት ነው! ንጥር የህይወት ቅመም ጥሑም የህይወት ቀለም የኑበስና የስጋ መንገሻ ዙፋንም ነው። ይህ የግጥም መድብል ስለ-ግጥም አይነትና ባህሪያት፣ ልዩነትና የልዩነታቸውን ምንነትን በማብራራት የሚጀምር አይደለም። እንደ-ጉድለት ካያችሁብኝ ከቀደምት ታላቅ ጸሃፊያን የወረደውን የፊደል ትንፋሽ ትስቡ ዘንድ ብጠይቅስ። ፍርሃቴ የኔ-ገለጻ ትንፋግ ይሆናል ብቻም ሳይሆን ቅጂም እንዳይሆን አብልጬ ስለምሰጋ ነው። ለዚህም ስል ከቀደምቶቹ ጸሃፍት የአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌን ወይም ያለቃ ታዬን ወይም ካለፉትና በህይወት ካሉት ከታላላቅ ጸሃፍቶች እና አንባቢያን ( የነብሴ መስታዋት ከሆነውና እጅጉን ከምወደው እውነትንም ካስተማረኝ ከባለቅኔው ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህ ወይም ከኔው ሰብአ ሰገል፣የብርሃን ፍቅር ተግዥ ከሆነው ኢምላከ ወይም ከሰሎሞን ደሬሳ ወይም ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ጉልህ አስተዋፅዖ በማበርከት ላይ ካሉት ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ፣የቋንቋው ጥንካሬ፣ ስብእናውና ውብ ህሊናው ( ተጽፎ ባገኘሁት መረጃም ቢሆን) ምን አለ ጸሃፍት እንዳንተ በሆኑ ከምለው ዩሃንስ አድማሱ... የውበት ግማድ ከሆኑት ገ/ከርስቶስ ደስታና ብርሃኑ ዘሪሁን ኢንዲሁም ለዚህ ለዛሬው ማንነቱ ጉልህ አስተዋፅዖ አበርክተው አልፈዋል ብዬ ከማምነው መንግስቱ ለማና ዶ/ር ከበደ ሚካኤል) የተከተቡትን መግቢያ መሰል ባለ-ጥልቅ ባህሪይ ሃተታ(በቅጥታም ሆነ በዝውር የተፃፉትን) አንብባችሁ ካወቃችሁ እጅጉን በቂ ስለሚሆን።

ይህንን የግጥም መድብል ለማሳተም ስደፍር ኹለት ነገሮችን ተስፋ አድርጌ ነው። ፩ኛው ስለ ነጻነት ያለኝ አመለካከት ነጻ ከመሆንና በነጻ ስርዐት ውስጥ ከመኖር ውጪ የተሻለ አማራጭ ስለሌለው ያንን-አየር ለመተንፈስ ካለኝ ድፍረት የመንጨ ሲሆን፣ ፪ኛውና የተለየ-የሚመስለው ካልጻፍኩኝ መኖር ስለማልችል ነው። ለዚያም 'ንደ-እማኝ ራይነር ማሪያ ሪልከን ብጠቅስ ማንነቱ ካገሬ ጸሓፍቶች ተከትሎ የመጣነውና "ይህ ነጭን የመጥቀስ አባዜ የያዘው ትውልድ" እንዳትሉኝ እየተማጸንኩ ቅርሚያዬን ቀንጭቤ አቀርበዋለሁ።

ይህንን ደብዳቤ ሪልክ የጻፈው "ለወጣቱ ገጣሚ ደብዳቤዎች"(Letters to A Young Poet) በሚለው መጽሃፉ ላይ ሲሆን፣ የያኔው የ 19 አመት ወጣት ፍራንዝ ካባዝ ሰለጻፋቸው ግጥሞች ለሪልክ ባቀረበው የምክርና የሂስ ሃሳብ ከሪሊክ ዘንድ ከተሰጡት መልሶች ውስጥ ለኔ የሚመስለውን ተዋስኩት።"፩ ነገር ብቻ ማድረግ ትችላለህ ወደ-ራስህ ተመለስ...'ንድትፅፍ ያደረግህን 'ውነተኛ ምክንያት እራስህን ብቻ ጠይቅ...(ውነትን)ካልፃፍክ መኖር 'ንደማትችል ምስክሩን ከራስህ ዘንድ ብቻ

አገዳን ከግቻ
ሲነጥል...ሲለያይ
የኔ አባት ገበሬው
አልቤኑ ነው አልቦው
ሰኔ ጎለጎታው
ማረሻና ወገሉ
ግማሽ ጎን አካሉ
'ሱ ነው እምነቱ
'ምነቱ ነው ቃሉ።
የኔ አባት ገበሬው
አሂዶ ያስሄደ
ጤፍን ያዘመመ
አደይ የቀጠፈ
የ'ዮሃ ለምለም ሳር ሰርዶ የዘነጠፈ
ግልገልና...ደቦል....አጣምሮ ያቀፈ
የኔ አባት ገበሬው
'ምነቱ ነው ሀብቱ
እምቢኝ ነጻነቱ
ነጻ ወንድነቱ
ያ ኑቢያነቱ
የኔ አባት ገበሬው
የኦፊር ስጦታ
የራማ ነጭ እጣን
የሰሎሞን...ህጣን
የሰብአ' ጥሪ
ውልደትን አብሳሪ
ተጉዋዥ በጨረቃ
የኩሽ ምድር ንጉስ
የ ግብጦች አለቃ





የኔ አባት ገበሬው
ነጻነት...አይነቱ.
የደሙ ቀለም ነው
እምቢኝ ወንድነቱ።
ሞትን የደፈረ
በመድፈር የኖረ
ኖሮ የተማረ
ላገሩ ነጻነት
ጥይት ለነብሱ ህይወት
አ ብሎ የጠጣ
ጠጥቶ....ያለፈ.
አልፎ የገዘፈ።
የኔ አባት ገበሬው
እሱን እመስላለሁ
እሱን እሆናለሁ
እምቢ....ዝባዝንኬ
ዝባዝንኬ ዘኬ
ላ'ገሬ ነጻነት
አባቴ ነው ልኬ
አባቴ ነው መልኬ.።

## ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም

በ-ቁንጽል ፍቅር ያልተወጋሁ
ጽንፍ የፍቅር መናኔ
ፍቅር "ንደ ኸረት የጮኸብኝ
የኢትዮጵያዊነት ምስለኔ
ረቂቅ:የንጋት መዝሙር
ለቂቅ :የብርሃን በር
አብ በአእዋፋት ልሳን
የሚከረከረው ክራር
ያ'ጥብያ ኮከብ በዠርባቸው የሚመጠምጡት ጠፈር
መንኩሳት የሚማልሉት የጣና ገዳም ቀመር።
እህል ቆልተው
ቀርከሃን ለብዕር ቀርፀው
ፍቅር እየነከሩ
አንድነት እየመከሩ
በብራና ላይ የመቱት
እመ ኑቢያ ከትብት
እሱን ማወቅ ነው እጣዬ





ማወቅ ነው የኔ ፍላጎት
የጥቁር አፈሬን ጉልበት
ሲገፉት የሚሸሽ ሳይሆን በሞት የሚጸና እውነት።
መሆን ነው...
በረጅም ዋሻ የሚያዝ
ሽንጡ ላይ የሚመረቀዝ
ፅልመትን አልፎ የበራ
ባህር ከፍሎ ህዝብ የመራ።

መሆን ነው የኔ ፍላጎት
ለታሪኬ ሙክራብ መሞት።
ከያዘሽ አሽከላ ለፈውስ
ግንባር፡ እናቴ ቢቆረስ
ቅንጣት ታህል አይቆጨኝም
"ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም"
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም!

እምባሽን ከሚፀነፅል
ስቃይሽን ከሚደልል
መጥፊያሽንም በአንቀጽ
ከሚከትብ ከሚፈድል...
ሃዘንሽ :ረብጣ ችሮት
እሱን ባንቺ ላይ አኑሮት
ለቀብርሽ ከሚማልል
ቃል ለምድር ለሰማይ
እኔስ ከሱ ጋ ላልታይ።
ገፅሽ በማዲያት ሲፈተን
እምቅ ጉልበትሽ ሲበተን
የወገብሽ ጥብቅ ሲላላ

ቅርስሽ በባዕድ ሲበላ
ድንበርሽ እየተገፋ
የክብርሽ ጠረን ሲጠፋ
መነኩሳቶችሽ ምስጋና፡ ማህሌትሽን ሲመከኑ
ከገዳማቱ ተገፍተው፡ ባደባባይ ሲበተኑ
በዘር፡ ማንነት ሲወሰን
ምደረ አዳሜ ክብርሽን፡ ንፅህናሽን ሲወስብ
ብርሓንሽን ሳይጠግብ፡ ልጅሽ በብራ ሲረሽን
ታሪክን ብቻ እያወሩ
ማ! ቢወልድ ማ! የዘር ግንድ
የንጉስ ደም እየጠሩ
የራስ- ራስ- ቁባቶች
ቅንጣት ታህልም ሳይጠሩ
ወርቅ ጨርቅየነገር ትንናግ
ጠራሁ ቆሽሽከ ከፉ ትንፋግ
ሰባራ አጥንት፡ምንትስ
የመቅኒ መግል ስንምግ
ወይጦ ባሪያ፡ገኸ ተገዢ
አሳላፊ፡ ኩራዝ ያዢ
የንጉስ ዘር አድሃሪ
ባፍ ይጠፉ ባወሩበት
'ራሱየትውልድ ጠር ፡ጥርሳም እሳ ነባሪ
ሶሻሊዝም፡ እንትኒዝም "የነጋበት አጭበርባሪ"
ማሌሊት፡ ሃርነት ትግራይ
የቂም ጉልበት፡ የቂም ታጋይ
ሌላ ጭፍን...ሌላ ድንጋይ።
ቅንጣት ታህልም ሳይጠሩ
የዘር በሽታ ሲያከሩ
ህሊናቸው ላይ ሸፍተው



ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም

ተደብቀው በሚኖሩ
በነሱ ቀንሽ አይመሽም
"ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም"
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም።
ሸማ የሸመንሽበት፡ የማይላላው ጥብቅ ክንድሽ
እንዝርትን ያሸረው እጅሽ
ቀፎውን በማር የሞላው
አክሱም ፅዮንን ያቆመው
የሃን ከግርሽ ስር ያነፀው
ለክብርሽ ሳባን ያስነሳው
ሰ'ብ- አ ሠገልን ያነቃ
ማር በሊታውን በስምሽ፡ መቅድስ እንዲያቆም ያበቃ
ስንዱ ፈቃድሽ የታል?
ውዴ ያንቺ ነውና
ሙሽራው ዛሬም ለስምሽ ለህልውናሽ ይሞታል።
ምድርሽ አደይን ሲቀባ
ያሬድ ቅኔን አገልድሞ
በወረብ መቅደስ ሲገባ
ህጣናቶቹ መስከሽ ላይ ቁግ እያስደነሱ
የቡሄን ጅራፍ ሲገርፉ
አበባ በምድርሽ አይተው
አበባ አየሁኝ ምስጋና
እነሱም ቅኔን ሲዘርፉ
የኖርሽው ዘመን ይመለስ
ብርሃን ምድርሽን ይውረስ!
ሀገሬው በሃገርኛ
ኬር ይሁን ይባረክ ያሉት
ጠቢቦች ኮከብ እያዩ
ደርሰው ደጃፉን የሳሙት

አንቺ የክብር እመቤት
መርአቴ የኔ ሙሽራ
አንቀጽሽ ከደጅ ቆሟል
ፍቀጂው ብርሃን ያብራ።
ካንቺ መኻጠን ተጥሎ
በ-ማእዶት በምስጋና...ሰርቅ ማህሌትን ቆሞ
ስጋውን ላንቺ በድሎ ጥቁር አፈርሽን ቅሞ
በማለዳ ይጠራሻል
ሙሽራው ከልፍኝሽ ይግባ
እቴ እሱ ይሻልሻል።
እናም ይህን እልሻለሁ
አይኑን በጨው የታጠበ
ነጻ ወ'ጥቶ የጠበበ
ከርስ ሆድ እቃው ተወጥሮ
የነብሱ ክር የረገበ
ውጭ አካሉ ተሰድሮ
ግንዛቤው የነተበ
ብልህነቱ የበላው
ታዛዥነቱ ያጎላው
ቆሻሻነቱ ያጠራው
አንቺን መሽጡ ያስጠራው
እኩይነቱ የገራው
ዛሬ ምድርሽ ላይ ቢነግስም
ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም።
ትናንት እንኩዋ በመስመሬ በስንኜ ስዘክርሽ
ያጨበጨቡበት መዳፍ ገና ሙቀቱ ሳይለቀው
እነሱ ከኔ ተሽለው ለዚህ ህይወቴ ተጨንቀው
"ምን የሰራል ቦጠሊቃ አርፈህ... ትምህርትህን ተማር!"





የሚል የባንዳ በገና ያውም "ባ'ለ አስራአንድ አውታር"
እንሱ ከበከቱበት ከፈተፈቱት ዘኬይቸው
ሊያውም ታ'ውሮጳና ታ'ማሪካ በተቋጠረ ምሳቸው
ይሄን የነገር እንግዴ
ደሞ እንዲደርሰው ለሆዴ
በሰለጠነ ልመና
"ምክር" በተባለ ዘዴ
ሲያንቆረቁረው አደረ... አዛኝ ተብዬው ዘመዴ።
"ቤተሰብ መስርት" ምናምን
ስንዱ እንዲህይለኛል...
ከዚህ በላይ ትልቅ ምክር አሁን ከወዴት ይገኛል?
አስር ቤተሰብ መመገብ
ለልጅና ለራስ ብቻ በራስ ዛቢያ መሽከርከር
እሱ ከሆነ መኖር
እሱ ከሆነ ሃገር
እንግዲህ ሃገር የለኝም
ወይ ሃገር የሚሉት ነገር ገና ዛሬም አልገባኝም
ወይም ያንቺን ህልውና
አላውቀውም አያውቀኝም።
ደሞም ስሜቴም በድን ነው
ያ'ድዋ የድል ደም እንጂ
ያ'ድዋ ወጥ የማይሸተው
ምኞት ተቀነባብሮ ባርነትን የማይግተው
የነዘርአይ ታርክ እንጂ
የነ-ዘር ላይ ዛር ያልሻተው
ይሕንን አንቺም ታውቂያለሽ
የኔ ስሜት ለዘር ድግስ
ለዘር ወጣወጥ በድን ነው
ከኢትዮጵያዊነት በታች መጥበብ አይችልም ስሜቴ

አርበ-ሰፊ ነው ቆዳዬ ማደሪያ የሆነው ለትበቴ።
ግና ይሄንን አውቃለሁ
ያጥፊና የቀጣፊ ልጅ
መውረዱና መዋረዱ
የማይቀር ነው ፈር ባስያዘው ባባቱ ዱካ መሄዱ።
ግና ይህንን በዘመኔ
በዘመነላቸው ዝሙን
ለከትን በተነፈጉ
ማኸጠንሸን በወጉ
በወተትሽ የወተት ጥርስ የግት መነከሻ ባወጡ
በቅኝ እጅ እየጨብጡ
በግራው እያደፈጡ
ሲደገፉ እያስደገፉ
ሲታመኑ እየለመኑ
መስሎ ማደር የተቀቡ
ለባርነት የመነኑ
በምድርሽ ዛሬ ቢነግሱም
"ሰው ኢንጂ ህዝብ አላጣሽም"
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም።
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም
ሞት ቢሆን እንኩዋ እጣዬ
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም
ጨላማ ቤት ውስጥ ተጥዬ።
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም
ቢላጩን ጥፍሬን ቢነቅሉት
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም
ስጋዬን ሜዳ ቢጥሉት።
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም
ጅብ ቢስቅ ሬሳዬ ላይ



ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም

በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም
ያንቺን ጥሩ ቀን ሳላይ።
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም
ተኩላ አጥንቴን ቢቀጠቅጥ
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም
ጥንብ አንሳ ቆዳዬን ቢልጥ
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም
ጥንትም ሰው እንጂ የሚቆርጥ
መንጋማ የህዝብ አጋሰስ.
ዛሬም ቢሆን አላጣሽም!
እኔ አልሸሽም አልታሽም
ለሆዴ አንቺን አልዋሽም
ለቀፈቴ ህሊናዬ ማንነቴ አይቆሽሽም
ለኩርማን መሬት ችሮታ
ግሳት ለሚሆን አለኝታ
ስቀቀን ለሆን ሹመት
ተንቀው ለሚከብሩበት
ራስ ደፍተው ግን ተሹመው
እላይ ሆነው 'ታች አድረው
ዘላለም ለማይኖሩበት
ሲያልፍ ለሚገለማ
በቁም  ውስጥን ለሚያደማ
ኢትዮጵያ ሙች እልሻለሁ!!!
ትግሉ ቢበረታም እንከዋ
የፍቅርሽ ሰልፈኛ አንሶ
ሁለት ዛፍ ላይ የተሰካውለስጋው: እውነቱ ረከሶ
ሻኛው ተከንብሎ ቢታይ
ሲወጣ ያ የውነት ጠሃይ
ይቀልጣል ቁጥርጥር ሞራው

ይወጣል ድብቅ ገበናው።
ኢትዮጵያ ህዝብ አላጣሽም
እናቴ ህዝብ አላጣሽም
ምናምን ሚሊዮን አለሽ
ያንቺ ማህፀን ባይዋሽም
ለዘመናት ባታርጪም
ዛሬ ግን ወንድ አልወለድሽም
የሚልሽ የሚቆምልሽ
በሞትሽ ላይ እኔ አልሽሽም።
በክብርሽ ላይ አልቆሽሽም
አልዋሽሽም አ'ላ-ምሽም
አልሸጥሽም አንቺ ሃገሬ
የሚልሽ ወንድ አልወልድሽም።
ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም
ወንድ እንጂ ጎረምሳማ አልሽ
ሃርሽ አደባባይ በምጽዋት በልመና እጅ ያቆመሽ...
ሰው እንጂ...





## ፊቴ ሽራ ሆና ትዝታን የሚስል

ሞትና ቅዳሴ...ነብስና ውዳሴ
ሰመዓት ሆንክና
ላስብህ ተነሳሁ...
በትዝታህ ግርሻ...
ውስጤን እያሳሳሁ።
ላስብህ ተነሳሁ....
ትናንትን ተርፌ
አንተ ለኔ ሞተህ
ካ'ንተ ሞት ዘለላ...እንጉዋን አስተርፌ
ስንኝ አራግፌ
ሞትህን ተጽፌ.
ፊቴ ሽራ ሆኖ
ትዝታን የሚስል
ፍጹም ከማያውቅህ
አዛኝ ከሚመስል
ተ-ልቅሶ ቤት ገብቶ
ፊቱን በመኃረብ...በጨርቅ ሸፍኖ
ለቅሶ ከሚያስመስል
ከ'ሱ ጋራ ሁኜ
ማህሌት ቆምኩልህ
በ'ንባ ጸናጽል
አንተ የኔ አላፊ
እኔ ያንተ ቅጽል።
ትዝ ትለኛለህ
የነበረህ ስሜት
ከበራሪው ጥይት...

ልብህ ውስጥ ያደረው
የ-ጠበቀው እውነት
ትዝ ትለኛለህ።

ዛሬ አንተ የለህም
    አንተ-የኔ...መስዕዋት።
እኔ ደሞ ቋሚ
ልክህን ገጣሚ
ለሞትህ ሰዳሪ
የቅኔ ዘራፊ
አንኙ-ና መቼትን
ለፈሰሰው ደምህ
ለነብስህ ጠላፊ።
ይኸው ጊዜ ከፉው...
'ኔ ቋሚ ሆኜ
አንተን አበው አር'ጎ
ያሳለፍነው ነገር ከደም ስሬ ሰርጎ...
'ምባዬ እየመጣ
እልኼ እየምጣ...
መሐል ላይ ትዝታህ ተንጦ እየወጣ...
ከግጥምም ግጥም
ሞ-ትክን ገጠምኩት...
የቋሚ ሟች ሆኜ
ትዝታህን ኖርኩት።
የ-ዘ-ጽዓት ልጆች...ነፃነትን ብለን
በንጹህ ልቦና ናፍቀን አዲስ ዘመን
ከ-ን-ዐን ልንገባ አ-ስ-ኩ-ዋ-ላውን ከበን...
መዝሙር ስናሰማ....
ደምና ጉዋጉንቸር





ቅማል'ና አንበጣፍቅራችን ነበረ ጠላትን የቀጣ።
የ-ዘ-ጸ-አ-ት ልጆች ነጣነትን ያልን
ኮ-ሮጆው ተቀዶ በደም የታጠብን....
ለዚያች ጥቁር አፈር ልጆ-ች-ዋ- ነብርን።
ልጆቿ ነበርን...
ተሰፋን የሰነቅን
በቀን- በጠራራ
በጥይት- ያለቅን።
ልጆቿ ነበርን....
ዘራችን ተቆጥሮ
እግርና እጃችን ፊጢኝ ተጠፍሮ
በየመታጎሪያው የተወረወርን።
ለጆቿ ነበርን
እየተረገጥን ሜዳ -ላይ ያደርን።
አሻጋሪው ነብይ
ህዝቦቹን ረስቶ
ለበርጩማ ጥጃ.... በወያኔ... ኮሬብ  ጽናቱ ተፈቶ
ሊያውም ትናንትና
በዚያ በጠራራ
የፈሰሰው ደምህ ካፈሩ ሳይጠራ
የሞትክ ትዝታ ገና ሳያባራ
ተ-ምርጫ ዘመቻ ተ-ርቅ አደባባይ
ድንኩ-ዋ-ኑን ሲተክል ተ-መቃብርህ ላይ
እሱን ተከትለህ መሞትህን ሳስብ...
አጥንቴን ቢበላኝ
ልቤ ውስጤ ቢላብ...
ትዝታህን ብራብ
አንተ አፈር ሆነህ....
ቀየው ላጭበርባሪ ሲሆን ለደላላ....

"እውነትም ሀገሬ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ!"
ከማለት በስተቀር ሌላ ምን እላለሁ
እንጂማ ለግዜ ዘመን ለመቁጠሪያ
ዘመንን ለመጥሪያ...
ማሰብ ሆኖን ስራ
መቶ አመት አልፈን ባድዋ ስንከራ።
አሁን ምን ዋጋ አለው ትዝታህን ባስብ
ገጽታህን ብራብ
ውስጥ አንዠቴ ቢላብ
አሁን ምን ዋጋ አለው
ጥቅስ ተሸከሜ... ጉልበቴ ቢራገብ
ወሬ ምን ያረጋል
ይቅርና ያንተ ሞት
በግ እንከ-ዋን ለኔ አልፉዋ
የኔን ሆድ ለመሙላት
'ኔ ግን ባዶ ነኝ... ያለተፈጠረብኝ የሚቆርጥ አንዠት
በብዙ መስዕዋት ቆሜ የምሄድ ከብት።
'ኔ አሁን ማ!...ይሙት
ምን ይሉኝ አሳቢ ምን ይሉኝ አዛኝ ነኝ
የሙታ'መትህ ቀን...ለ-ዝከርህ ስገኝ።
እኔን ብሎ አሳቢ...
ከመቃብርህ ላይ ድርጅት ጠራቢ
ከፈሰሰው ደምህ ከሞትህ ቀራቢ
ግለኝንት አብቃይ... ዘረኝነት አርቢ
ያንተ መስተውድድ... ያንተ ተደራቢ
እኔን ብሎ አዛኝ...ማ! ይሉኝ አሳቢ።
ከበጎቹ መኀል ጠፍቼ ያልተገኘሁ
በ-ዝከር ያድዋን ቅኔ የተቀኘሁ
ከፍርሃት ዋሻ





ከክህደት ጢሻ
ጭራዬን ስቆላ እንደ ሰሎግ ውሻ
ሙ-ሰዋት ያቃተኝ
እኔ ነኝ ኑቢያ... እኔ ነኝ ኢትዮጵያ እኔ ነኝ ሓበሻ!
ወገኔ ሲደማ
ስሙንና ክብሩን
መሬቱን ሲቀማ
ከቀዬው ሲገፋ
አንገቱን ሲደፋ....
እኔ ግን በሩቁ ስምህን ወርሼ
ክብርህን አርክሼ
አለሁኝ እያልኩህ...
'ኔ ያንተ አሳቢ የተዝካርህ ደራሽ
ለትዝታህ- ዕልፍኝ ተከራይ አዳራሽ...
አንተ ለኔ ፈራሽ....
ይህን ህይወት ብዬ መሞትን ፈርቼ አጨበጭባለሁ
አዳራሽ ዘግቼ።
ይህን ህይወት ብዬ...
መሆኔ ሳይገባኝ የታርከ ዱርዬ...
አመት እየቆጠርኩ...
እላልሁ እዬዬ።
እናም ዛሬ ርቄ
አንተን ለመዘከር ግጥም ተጠይቄ
ሊያውም ለወንድሜ
አብረን ለተራብነው
ካ-ውሬ የተረፈ አካል ለቀበርነው
ምን ያረጋል ግጥም
አፈር ላ-ያነሳ
መሆንን ያቃተው በስራህ ሊነሳ።

ምን ያደርጋል ቅኔ!
ምን ያደርጋል ወሬ!
'ኔ 'ንተን ቀብሬ!
ታገር ተባርሬ!
ትዝታን ድንብሬ!
ምን ያረጋል ግጥም!
ምን ያ-ረጋል ወሬ?
ግጥምስ መጋጠም...
ነው እንጂ መፋጠም....
እሱ ነው መዘከር
እሱ ነው መፈከር
መመለሻ-ያንተን ደም።
ወሬ ምን ያረጋል
ርቀው ቢያስቡህ...ተመቃብርህ ላይ... ትልቅ ሙጃ
ያድጋል።
ማስብስ እሱን ነው... ሊማ-ሊሞን መውረድ
እንዲህ ተበሻቅጦ ቆሞ ከመዋረድ።
ማሰብስ እሱን ነው... ፉኖ ፉኖ ማለት...
እንዲህ ተኮፍሶ... እንዲህ ተኳኩሎ በሱፍ...ተጠቅልሎ....
ታሪክን ከማብከት...
ሰው ሆኖ የቁም ከብት
የሚንዳ መንጋ...ማንም የሚያዝበት
ይሻለኝ ነበረ አጠገብህ ብሞት!
ሞትህን ከማሰብ ምናለ ትግልህን ፋናህን ብከተል...
አድዋ ላይ ቁንጽል ጭራ ከምቀጥል.....
ምናለ-ብከተል?!
ይህን ዘረኝነት...መንደርተኛ ስሜት..
ከውስጤ ብነቅል...
የድል ቀን ባሰግር



ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም

ምናለ ሞትክን ፋናህን ብከተል።
ወገኔ በረሓብ...ሬሳው በሸክም...ሲነሳ በሳንሳ...
እንዲህ  ተሰብስቤ ከምሆን አስተዋሽ የሞትህ ቃሬዛ
ምናለ ሞዜሬን   ዝናሬን ባነሳ።
እናም ዛሬ ርቄ...
አንተን ለመዘከር ግጥም ተጠይቄ...
ቃላት እፈትላለሁ...
ሞትህን ዘርፌ...
የጭብጨባ ኩታ... ቡልኮ እለብሳልሁ....
መች ይሆን እላልሁ...
መቼ ይሆን ዘካሪ ተ-ዘካሪ ሆኖ....
የሚኖረው ሞቶ... በመሞቱ ገኖ!
መች ይሆን እላለሁ።
መች ይሆን እላለሁ
ታሪካችን ገብቶን...ከ-መዘከር ወጥተን
ለ-መዘከር በቅተን...
በልጆቻችን አፍ....በክብር ተጠርተን
የምኖረው ነጽተን...ለ-ዘመናት ጠርተን
መች ይሆን እላለሁ?...

መች ይሆን አስታዋሽ....
የሚበቃው መሸሽ....
መች ይሆን አንዣርቱ...
ጩኸት የሚያቆመው...በፈሰሰ አሞቱ...
መች ይሆን ዘካሪ ተ-ዘካሪ ሆኖ
የሚኖረው ሞቶ....
በመሞቱ ገኖ...
...መች...ይ-ሆ-ን
እላለሁ

## ንገሩን መቼ ንናደድ

የሰከነ የፍቅር ትንፋሽ በደሜ ወስጥ ስላደረ
ያንቺን የበረከት ቃል ልቤ ፍቅርሽን ኖረ።
እንደ-ቀንድ አውጣ ሳልቧችር
ሳልጠቀለል በሆዴ...
የጫት እንጨት ሳልታጠቅ....ሳይሆንኝ ኮባ ጎራዴ.....
ማተቤን በጥሼ ሳልጥል
ሳይሆንኝ.....ከፋት ዘመዴ
ትናንትሽን ካድማስ ምዶ
ጠፈር ገምሼ ሳማትር....
ስምሽ በከፉ ሲነሳ....ፊቴ ግንባሬ ሲቋጠር.....
የድል ዘመንሽ ሃቅ ሆኖ ከፊቴ እየቀደመ
የሚሉኝ ሰምቶ ሳይሆን
አንቺ በሆንሽው ታከመ።
አለም...
ግማሽ ነባራዊ ሃቅ....የምር መድረክ ሆኖ
ገጸ-ብህሪይ በፈርጁ...በየመስኩ አሰልጥኖ
ት-ወና-ውን እንዲጫወት አንዱን ቀማኛ ሲያደርገው...
ሊያውም ከራሱ ማጀት ከራሱ ኪስ የሚሰርቀው.....
ሰው እንዴት ሽሉን ሲበላ....አንድ ግዜ እንኳዋ
አያነቀው?....
ጊዜው ሲያልፍ ማንነቱም...ምንነቱም አብሮ ሊጠልቅ...
ዛሬ መድረኩ የሱ ነው...ተዉት እንዳሻው ያውራ....
...ድንቁርናውን ይራቀቅ።





እናም ዛሬ እንደምታውቂው...
መሬቱን ብቻ አይደለም
ህዝብሽ ምሬቱን ተነጥቋል...
ወንድነቱም እንደ "ቅልም ልብስ"
ለሆዱ ሲያድር ለቋል።
እናም የሆነው ቢጨንቀኝ....
የንደምን ሆነ ይህ ነገር.....የጥያቄ ቃል አነቀኝ።
ይህንን ነደፍኩኝ ላንተ.....
በል ልበልሃ ወገኔ....
አውጫጭኙን ጭኜ መጣሁ...."እንደምን ገዛህ ወያኔ?"
ሃገርህ እንዲህ ትላላች....
ይህንን ጥያቄ ስማኝ....
እንዴት ያንተ ወንድነት እኔን እናትህን ይጥማኝ?
እንግዲህ ዝምታ በልጦ
እንደምስጥ ካ'ፈሩ ስር
ከጨለማ ውስጥ ተቀብረን....
ወይ ሙተን አልበሰበስን
ወይ ቁመን አልተነፈስን....
ውይ ስበን አልተፋሰስን...
መልካ አድር-ባይ ውዳሴ....
የማንቦት ሃያ "ጎሎጎታን"
ቀበሌም መቆም ግብር ሆኖ....በስፍር ስኳር ተረታን።
እራሳችንን ፈንግለን...
ተሰብስበን ስንዋረድ....
እስኪ እንግዲህ ንገሩኝ...መቼ በርሃ እንውረድ?
ግራ ገብቶኛል እኔ.... እንግዲህ መቼ እንናደድ?....
ወይ እንነጋገር እንዴ ንዴት ምን እንደሆነ?....
ሰው በቃኝ መቼ እንደሚል....ማ'ስ ጀግና እንደነበረ.....
እንነጋገር ንገሩኝ....እምቢኝም ሲቆይ ይረሳል....

ነጻነት "መጣሁ መጣሁ " ሲል
ፍንግል ነብስ ድሮም ያሳሳል።
ቀን ቁረጡና ንገሩኝ...መቼ ግፉ እንደሚበቃን...
ምን አይነት ንቀት ይሆናል....ካለንበት የሚያነቃን?.....
ቀን ቁረጡና ንገሩኝ....
አውድማው....ባድማ ሆኖ.....
ሀሩር ምድሩን እየመታው....
ረሃብ ወገቡን ታጥቆ....ቀዬ መንደሩን ሲንጠው....
ወንድ እናቱን ከነ-ራቧ.....ከነስቃዩ-ዋ ጥሎ.....
ሃገር ጥሎ ሲኮበልል....ጎለፈቱን አንጠልጥሎ.....
ተስፋውን ለትንሽ ጀልባ...ለሚንገዳገድ ቀዘፋ
ጸሎቱን ለውሃ ጥፊ....ለውቂያኖስ ላይ ቀፈፋ....
ሮም ከነዓን ሆኖ....አድማስ ሲያማትር በተስፋ...
ሃገሩን ለጀርባው ስጥቶ....ረጅም ውሃ ሲገፋ....
ለዘንድሮው ያገሬ ሰው ....ነጻነት ወይ ክብር ማለት...
ጥልቁን ውሃ እየቀዘፉ...መሞት ነው በውሃ ጭነት።
ነጻነት ማለት ህልም ነው....
ነጭ ወረቀት የሚሞሉት
ጀግንነት ሆነ ፍንገላ...እራስን እጣ የሚጥሉት።
ነጻነት መናሳነስ ነው....በገላጭ የሚገኝ ቀመር
ሊቀ-ሊቃውንት አከሌ....ብቻውን ለራሱ ክብር።
ነጻነት ዶፍተር መሆን ነው...
ጥበብ የጥበብ አውታር...
ስመ ተክህኖት ደርቦ....ለስደት ሰልፍ መገተር።
ነጻነት....ዝም ማለት ነው....
ዝምታ ያነቅዛል እንጂ
ድሮም....ዝም መች ነቅዞ ያ'ቃል....
እንደማሽላ ነው እሱም.....እያሳረረ ያስቃል።
እና ንገሩኝና.....ተሰብስበን እንናደድ....





ባፍጢማችን ተደፍተን ተዘቅዝቀን ከመዋደድ።
ንዴትን ጾመን ከሆነም....
ንገሩኝ ምንም አይደለም....
ትንሳኤ የሌለው ፍልሰታ....ድሮም ቢሆን አልነበረም።
እና ንገሩኝ በሞቴ
በየስርጡ ተወሽቀን....
እራሳችን ላይ በሽቀን....
የሚሉንን እየደገምን....ሆነን ከምንሞት በቀቀን....
ምነው ያኔ ስንወለድ....እትብቱ ታጥሮ ባነቀን።
አልያ አትደስኩሩ.....
እብቅ ትንፋሽ አታምቁ....ህሜት ነገር አታክርሩ....
ዝም ብላችሁ ተገዙ.....
ዝም ብላችሁ ዘንድሮም እንድትናንቱ ታረዙ።
ያደለው ሃገር ይይዛል....
ችዋዴ ግን ከንደ-ብርቱ ነው
እርጥብ ቅጠሉን አጣምሮ....እግሩን ቆልፎ ይመዛል።
እና እባካችሁ ንገሩኝ...
መቼ ይሆን የሚበቃን....
ምን አይነት ንቀት ይሆናል ካለንበት የሚያነቃን
እስኪ ሁሉን እርሱትና.....
አንዴ ብቻ እንናደድ.....
ባፍጢማችን ተደፍተን ተፈንግሎ ከመዋደድ....
በቃኝ በቃህ በቃሽ ብለን....እስኪ በርሃ እንውረድ

## ገበሬው ምን ነካው

ገበሬው ምን ነካው...ወገኔን ምን ነካው
መሬቱን በጣቱ በጋቱ ሲለካው
ዘመዴን ምን ነካው
በኢዛና ጥበብ የፀናች ሃገርን
በቴዎድሮስ ትንፋሽ የቆመች ሐገርን
በጣይቱ መቀነት የፀናች ሐገርን
በበላዩ እንገት የኖረች ሐገርን
ለምለ ሟን ለምለምነ
ለምለሜን ሽጠዋት
እንኩዋን ልምላሜ ...ዛሬ ስምም የላት
እንኩዋን ልምላሜ....ዛሬ ሰውም የላት።
ያቺን... የኔን ሐገር
የስልጣኔን በር
የጥበብ አሻራን
የድል መመሰያን...
አፈርን...አፍሪቃን አፍርን አፈርን
መፈጠሪያ ምድር
መከተቻ መንደር
ያቺን ትልቅ ሐገር....
ለምለሙዋን ለምለምን
ለምለሜን ሽጠዋት
እንኩዋን ልምላሜ ...ዛሬ ስምም የላት
እንኩዋን ልምላሜ....ዛሬ ሰውም የላት።
አይነት ዕንጂ ብሶት ነገር ፈታይ ጉዶች





መቼ ሰው አፈራች?
ዘመናት አለፈ ወንድ ከፀነሰች።
ወንድ አልፀነሰችም
ወንድ አልወለደችም
ባሩድና ጋሻ ሲጋጩ አላየችም
አርሱዋም አልኖረችም
አልተፈጠረችም።
እስኪ ተመልከተኝ
እታች ወርደን እንሰን
መጽናታችን ታሞ መጥራታችን ቀድሞ
እታች ወርደን አንሰን
ሽንት ስንመነዝር
እትንት ስንቆጥር...
ምን ነኩቶን ምን ነኩቷት
ወንድ ያላፈራችው ያልተፈጠርንባት?!
ዘመዴን ምን ነካው
ምን ከፋ አገኘብኝ
የምን ጥላ ወጊ ጥላውን ጣለብኝ።
ምን ነካው ገበሬው
ምን ነካው ወጣቱ
መሰደድ ነጻነት ሲሰደድ መሞቱ?
ሠደድ!... ነው መሰደድ
በቁጭት መባዘን
በሰቀቀን መንደድ!
ሃፍረት ነው ባርነት
ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለሆድ አንገት መድፋት
መሞት ነው ፍርሐት!
ምንድን ነው ፍርሐት?!
በራብ እያለቁ ብረት አለማንሳት።

ቅንቅን ነው መታገስ
ባህር ማዶ ሆኖ...ማየት ሐገር ሲፈርስ!
ዘኬ ነው ደሞዙ
ጥንብ አንሳ ነው ውርሱ
እከክ ነው ምኞቱ
ከል ነው ውበቱ
መሞት ነው ህይወቱ።
ዕብደት ነው መስማማት
ሃገርን ከሸጠ ከቅጥረኛ ባንዳ
ገበቴውን ከቦ የዕርቅ 'ራት መብላት
የዕርድ ራት መብላት
የቴዎድሮስን ስጋ በጥርስ እንደማንሳት
አሉላና ጉግሳን በከፉ እንደማንሳት።
ሃገሬው ምን ነካው
ሀገሬን ምን ነካት
ወንድሜን ምን ነከቶት
የ'ጃዙር ቀኝ ግዛት ወንድነቱን ፈቶት
ፈቶት ተፈታትኖት
ትከሻውን ሰብሮት
ምን ነከቶት ያየኛል
አንገትህን ስትደፋ ወንድሜ አትመስለኝም
አጥንቴን ባልቆጥር
ቢቀር ይሻለኛል።
ወገኔን ምን ነከቶት
የወንድነት ልቡ ድባቡ የረገፈው
ዝናር መታጠቂያው ወገቡ የሰነፈው፡፡
እሡን ምን ነከቶት ነው
ውሐ ውሐ ያሰኘው
በህለሙ እንኩ'ዋ ሲሞት





በላብ የረጠበው።
ነቅቶ በትዝታ
በቅዠት ትውስታ
ተኝቶ መሞቱን ህለሙን እያሠበ
ቁሞ እንኩ'ዋ እየሔደ በላብ የረጠበ!
ንቀትና ትዕቢት
ድንፋታና ዕብሪት
እንደ ሰኔ ሰማይ...መብረቅ እን'ዳረሰው
ገፁ በመከራ ማዲያ'ት የለበሰው
"መቻልን ለቻለ ቁሞ ለሄደ ስው"
ድንቄም ተረትኛ
ተረትና ነገር
ክብሩን ላይመልሰው
ይሄን የኔ ሀገር ሰው
ወገኔን ዘመዴን ወንድሜን ምን ነካው?
ምን ነካው ገበሬው
ምን ነካው ወጣቱ
የታል የሰማነው የታል ወንድነቱ?
የታል የሰማነው
ጥንት የተነገርነው
ከመተማ አድዋ
ከዶግ'አሊ ማይጨው
ይህን ታህል ሞተ
እንትና ሲዋጋ ከብሬን ብሎ አለፈ
በገዛ ጥይቱ ነብሱን አሳረፈ።
የታል የሠማነው
ከዋርካ ስር ሆነን ሾላ ዕየለቀምን
የሰማነው ታሪክ የሰማነው ዘመን
ታዲያ የታ'ል ዛሬ

የታ'ል ትናንትና
ወንድነት ስንገድፍ ሲገለጥ ገበና
ምን ነካን ከማለት ሌላ ምን አለና።
ምን ነካው ወገኔን
ምን ነካው ዘመዴን
ሲገዛው ቅጥረኛ
የታሪክ መደዴ.
የት ሔደ ዝናሩ
ግፍ አልፈታም አለ
የሸንጡ ጎራዴ?
ያኔ ትናንትና
ሠው ቢሉት ሠው ነበር
ሊያውም የጎጃም ሠው
ላገሩ ነጻነት ደሙን ያፈሰሰው።
ሠው ቢሉት ሠው ነበር
ሊያውም የጎንደር ሠው
በጎራዴው ስለት
ጦሙን የሚፈታ ጦሙን የሚያፈረስው።
ሠው ቢሉት ሠው ነበር ሊያውም የትግራይ ሠው
"የዘንድሮን ትግሬ" ያልሆነ መንፈሱ
የሚኮሰኩሰው ሐገሩን በመጥፎ በከፉ ሲ'ያነሱ።
ሠው ቢሉት ሠው ነበር
ሊያውም የሸዋ ሠው
ከመንዝና ግሼ
ጅባትና ሜጫ
ከጀማ ወንዝ ዳር
ከአሼ ውሐ ስር
የበቀለ ለምለም
የሰማይ ስንበሌጥ





የብርሐን ሸፋን የብርሀን መውጫ።
ሠው ቢሉት ሠው ነበር
ሊያውም የወሎ ሠው
ካ'ንባሠል ከባቲ
የፈለቀ ቅኔ.
ያላሊበላ ፍ'ቅር
በፍቅር የጣለው
ያሬዳዊ ዜማ......የፍቅር መከተቢያ
የፍቅር ጠመኔ.።
ሠው ቢሉት ሰው ነበር
ቦረን ከቦረና
ሶረን ከሶረኔ።
ወገኔ ነበረ
ሀገሬን ሐገሩ
ቤቱን የሚል ቤቴ
የደብረ-ታቦር ሰው
ያ'ማራ ሳይንቴ...
ሊያውም የጋይንቴ
ሊያውም የ-ይፋቴ
ሊያውም የ ተጉለቴ።
ሠው ቢሉት ሠው ነበር
ያውም ከ-ጎራ-አ-ጌ
ሊያውም ከ-ዐምባ-ላ-አ-ጌ
ሊያውም ከ-ወል-አ-ጋ-
ሊያውም ከ-ጅጅ-አ-ጋ-
ሊያውም ከ-ወል-ቂ-ጤ-
ሊያውም ከ-ወል-ቀ-አ-ይት-
የሰጠ ነበረ ግንባሩን ለጥይት።
አሁን የታል ጎን-እደር-

"የዘንድሮ ትግሬ!"
ዛሬ የታል ጅፋር
ዛሬ የታል ጅማ...
አልማ-አልማ-ትልማ
አውሮጳዊ ድርሰት-
የአድዋ ቅኔ
የራማ የደብ ድብዳብ
ሰሜናዊ ዜማ!
አፊዴን-ኢፊዴን-ብአዴን-ድድዴን-
ምን ነካው ወገኔን
ምን ነካው ዘመዴን?
ሃፍረትን በኔ ውስጥ
ፍርሃትን ባንተ
ለከህደት ቆመን
በኔ ትብስ ባንተ
እድሜያችን ቃተተ።
ወንድሜ ልንገርህ...
መሞትን ነቅተናል
መኖርን ሙተናል
የከህደት ጀግኖች
ታጋዮች ወጥቶናል።
የምትልንም ሰው
ህይወቱን በሞቱ...
ሞቱን ደሞ ዛሬ ለኛ በመሞቱ
እኛን ቆመን ሲያየን እሱ ዛሬ ሞቱ'ዋል
የረገፈ አካሉ
ያ'ፍረትእንባ አኧርቷል...
የምስጥ እንባ አንብቷል።
ያድዋ ነፍጠኛ...





በኔ በርካሹ በታሪክ ቁንጠኛ....
'መኖር ሲሞት አየሁ....
ዑመር ሰመተርን
አውራሪ ወራሪ ጀግና ሃብተጊዮርጊስን
ዘራ'ያአቆብና እና ልጅ ልብነ ድንግልን
አጼ ዮሐንስን
እነ አብዲሳ'አጋን አብርሃም ደቦጭን
ሞገስ አስገዶምን
ንጉስ ሚካኤልን...
ኮዋ ጦናንና ጅማ አባ ጅፍርን
በተራ በተራ
በኔ አንገት መድፋት ስር
በዘመኔ ክብር በገባርነቴ
በባርነቴ ግብር
ሁሉንም ቀበርኩኝ
ምን ነካው
ምን ነካኝ
ምን ነካን...እያልኩኝ
ሁሉንም ቀበርኩኝ።
እኔ ዘመነኛው የታሪክ ቁንጠኛ
በልመና ባጀት
በስልጡኑ ጎጆ... በባርነት ማጀት
እምብርቴን ቀፍድቼ
የቁም ሞቴን ሙቼ....
ገደልኩት ታሪኬን
ቀበርኩት ዕውነቴን።
በልመና ሚዳይ
ክብሬን ዘነጋሁት...
ገደልኩት ታሪኬን....

"አታውቀኝም ወግድ!"
"በምን ተገናኝቶ ያንተ ከኔ መንገድ"
"ያንተ ለኔ መንደድ"።
ሽቀልኩት ር'ስቴን
የማይነጥፍ ክብር
ኢትዮጵያዊነቴን።
ባርነት ሐርነት
ሐርነት አርነት
ልክ እንደ ስገራ ተቀላቀሉብኝ
አቤት ያንተ መዓት።
አቤት! ያንተ ስራ
አቤት ያንተ ቁጣ
ያ! የንቁላል አሽከር
ዳጉሳ ቸርቻሪ
ንጉስ ሆኖ መጣ።
እንኳን ለኔ ጌታ
እራሱን ከችጋር ከተገገርነቱ
መቼ ነፃ አወጣ?
አቤት ያንተ ቁጣ!
ለኔ ዘመነኛው የታሪክ ቁንጠኛ
ንጉስ አ'ር-ገሀ ሽምኸው
ያገሬን ደመኛ።
ብቻ ከራሴው ጋ'...እንዲሁ ስመካከር
እንዲሁ ስነጋገር...
ጥርሴን እያፋጨሁ
ጥርሴን እያጋጨሁ
ወገኔን ምን ነካው
ዘመዴን ምን ነካው
እንዲ'ህ እያልኩ ነው!





ይህ የኔ ባላገር
ሃገር የሌለው ገር
ምን ቀርው ከስሙ
ከመጠሪያው በቀር
"ባለ-ሐገር"...
እስቲ አሁን ምን ቀረው?
ከብቱን ከፉ "ደስታ"...በሽታ ሲቀማው...
የታጠቀ አሽከር ካደገበት ሠፈር
ከቀየው ሲገፋው?
ቆራጡን ባላገር ዘመዴን ምን ነካው?
አልማልኩኝም እንዴ?
ብከዳሽ አይቅናኝ
የምድርሽን ፀጋ የነገን ብርሃን
አምላክ አያሳየኝ
አላልኩሽም ነበር?
ዋሽቼ ሸሽቼ
ከድቼሽ መኖሬ
መሸተት ይሁንብኝ
ቅንቅን ይሁንብኝ...
አላልኩሽም ነበር
ትናጋዬ ይጣበቅ
ቆዳዬን ለምጥ ይምታው
አንቺን ለበደልሽ ለሞትሽ ከምተው
አልማልኩኝም ነበር?
ይሁንና እንግዲህ
ማህላዬ ይታደስ
ማህተቤን ልንከስ።
ባሩድና ጋሻ ...
...ፈረንጅና ሃበሻ...

በትግራይ ተራሮች በአድዋ ዋሻ....
ያጣፈውን ቅኔ....
የደሙን ጥቀርሻ....
የሚቆመው ዲያቆን
የሚዘርፈው ካህን
እኔና አንተ እንሁ'ን!
እኔና አንተ ዕንሁን ..."በረሃ ወረደ!"
ብረት የሚቀማ ጀግና ተወለደ!
እኔና አንተ እንሁ'ን
ዝናር በወገቡ
አነጣጥሮ አንጣሪ
ጋሻ ለወገኑ!
እኔና አንተ እንሁ'ን
አንተ እና እኔ ብቻ
የነፃነት ፈትል ደጋን ማባዘቻ።
እኔና አንተ እንሁ'ን
ገጥሞ የሚረታ
አልሞ የሚጥል
መቅኒ የሚፈታ።
እኔና አንተ እንሁ'ን
የፈረሱ ጌታ...
እርምጃ የሚመጥን ምፃት የሚገታ።
እኔና አንተ እንሁን...
አንተ እና'ኔ ብቻ....
"ገበየሁ ቢሞትም ተተክቷል ባልቻ!"
እኔና አንተ እንሁን...ታሪኩን አወቀ
ጠላቱ ሬሳ ላይ ፈረሱን አሳቀ።
እኔና አንተ እንሁን በርሃ ወረደ
ብረት የሚቀማ ጀግና ተወለደ!!!





## አንቺ ሀገር

ነጋልኝ እንደ ትናንቱ...
ስምሽን ልጥራ ውቢቱ
አንቺ ሃገር!
ማዕዷ...ድርሳንሽ ሆኖ
ታሪክሽ በውስጤ ሰፍኖ...
ዛሬም እንደ-ትናንቱ....
ስምሽን ልጥራ ውቢቱ
ኢትዮጵያ።
በመለከትሽ ከንቅልፌ
ደሞ ሲነጋ በደውል
ከምህሌትሽ ቀፍፌ
በንፅህናሽ ከውሽት...ካድርባይነት ጠፍፌ
ፍቅርሽን እሽርባለሁ...ጣቴን ለብእር ቆልፌ
አንቺ ሃገር።
ገሞራው የፍቅርሽ ስለት
ንፂት ብፅኢት ውበት
የናፍቆት የትዝታን ምጥ...ዘንድሮም ውስጤ ካነባ
ስንኜ አስራት ይሁንሽ...ስለቴን መጣሁ... ላስገባ።
...ኢትዮጵያ።
ጥቁር አፈርሽ አርግዞኝ
ለምለም መሃፀንሽ ይዞኝ
ልቤ አንቺን መርሳት አረጠ

ክብርሽን ብሎ ቆረጠ
ሃገሬ።
ዛሬም ካለሁበት ሆኜ... ከሚንተገተገው መብራት
በህግ ከተቆለፈው...ፍቅርን ከሞተው ስርአት
አናቴን የኮረኮመኝ
የሾላ ፍሬሽ ተግሳጽ
ምህዋሬ ላይ በጻፈው በከተበው ያንቺነት ቅርፅ
ፅንፍን ከሚሚስለው ውበት
አህዛብን ከሚነድፉበት
ከተሰማሙመብት ባርነት
ተሻለኝ ያንቺ ድህነት
ሃገሬ።
ለምለም አፈርሽ እትብቴን ከናቴ የተቀበለውየ
የመፈጠሬ ብስራት ያንቺ የመሆኔ ቁርባን ነው።
አውቃለሁ።
ለክብርሽ
ብለው ያለፉት
ከነ-ክብራቸው ያረፉት
ያለ-መጫሚያ የወጡት....የዘለቁትን አቀበት
ያለ-ስንቅ የደፈሩትን: የተጋጠሙት ክብረት
ታሪካቸው ይኸው ዛሬም ዘመናት አልፎ ይሰማል
በፈሪ ዘመን መጥቼ ልቤ ጀግንነት ይጠማል።
...ኢትዮጵያ።
እርኩስ ሊያረክስሽ ሲያሰልስ
ቀለም ጠገቡ ሲያቀልስ
የተሸከምሽው ህዝበ አዳም በነሲብ ሃሞቱ ሲፈስ
ወንድ ለንፅህናሽ ለክብርሽ መቆጠር ፈርቶ
መሲና ሲታረድልሽ ዛሬን መኖር ልቡ ሽቶ
ከተፈረከሰ ቆየ ሙከክ ካለ ጉልበቱ





ሃሞት እንዳቀረሽ ኢንደተላበ አንዠቱ
አንቺ ሃገር።
ጀግና ያረግዝሽበት
ያ! መሃፀንሽ ተረታ
ሰማይ ላይ የተሰየመው ድንቁ ሰንደቅሽ ተፈታ
በክብር የከበርሽበት ደማቅ ዘመንሽ ለቀቀ
ምሰሶሽ ምስጥ መሰጠው; ቤትሽ ከዳኑ ወደቀ
...አንቺ ሃገር።
ባእዳን በወለድሻቸው በቤትሽ ሎሌዋች መጡ
አድዋን ባድዋ ልጆች ያድዋን ተስካር ሊያወጡ....
...አንቺ ሃገር።
ፍርሃት ወንድነት ሆነ
ቸነፈር እድገት ተብሎ...ለሃያ አመታት ሰፈነ...
በ-ማጀትሽ የነገሰው ...ተው የሚለው ወንድን አጣ...
ይሄ የታሪክ አንበጣ...ሰብልሽ ላይ ከንፉን አወጣ...
...አንቺ ሃገር።
የጥበብሽ ዘርፍ ጥለቱ
ውበቱ ነበር ጋምቤላ
ዛሬስ ጥበቡ ተፈቶ ቀየው የህንድ እሳት በላ።
ደንሽ ይመነጠራል...
ደቡብ የወርቅ አፈርሽ በአረብ ወንፊት ይጠላል...
ልጅሽ እየታረደ በየ-ገደሉ ይጣላል
ይሄ ያልገባው የዋህ...ባባይ ስም ዕቁብ ይጥላል።
አንቺ ሃገር.....።
ደንሽ ይመነጠራል...
በስምሽ እርኩስ ይጠራል....
መዛግብትሽ በጨላማ....ባህር አቁዋርጦ..ይጋዛል
ቅዱሱ ጽላትሽ...በሎጥ....በአኖን መዳፍ ይያዛል
አንቺ ሃገር....አይይይ ያንቺ ስቃይ።

## መለከተ እምቢልታ ያበው እምቢልታ

ቃል የምነት እዳ እንጂ ያባት አይደልም አሉ...
ታዲያ እምቢልታ...አንተ መለከት....
የማን እዳ ይሆን አንተን -ያረገህ የአበው ጉልበት።
እምቢልታ ስርቅርቅ ብትር...
ይኸው ባንተ ነው እምታማው...
ይኸው ባንተ ትብታብ ነው...ካንተ በሆነው......ደሜ
....የቀን ጅብ መንበር አግኖት...ምንትስ...ያለኝ አዳሜ።
እምቢልታ...ነበልባል ግማድ....
ያበው የፍቅር ዜማ....ያበሻ....የስትንፋስ ሞገድ።
እምቢልታ....ማን ነበር ያኔ.....ስንቅ ላልያዘ አርበኛ
የጉልበት የትንሳኤ ክር....የድምጽ የመርገብ አፍለኛ
ማን ነበር....ከታቦቱ ፊት....ያንተን ድምጽ... እያስተጋባ
ማን ነበር ...ከፍም ከሳቱ...."እምቢኝ!!"...እያለ የገባ?
ማን ነበር?
ማን ነብር የዜማው መቅረዝ....
ማን ነበር "የበለው-በለው":የዘራፍ የእምቢኝ-መገኛ
ማን ነበር የማንነት ወንዝ
ማን ነበር....የምንነት ወዝ።
እምቢልታ...አነተ የአበው እምቢታ
ዛሬ ልጅህ....ለነጭ ዛር- ለምንዛሪ ተፈታ
ድጉዋን ቅኔን ....ውስጡን ሸጦ....በባእድ ቃል እፉን ፈታ።
እምቢልታ...





ማን ነበር ጋፋት ተገፍቶ
ባንተ አቀበት የወጣው....
ማን ነበር....ሽጉጡን መዞ.....እንደ ውሃ ጥም የጠጣው
ማን ነበር.....አንተ ታውቃለህ
ዛሬ ዝም ብትል ቅርስ ሆንህ
የአውሮጳን ሙዚየም ብታደምቅ
ስርቀቅታህ ላይታመቅ
የነጭ የባንዳ ከናፍር...ከድምፅህ ጋ ላይታረቅ
እንደምን ያለ ዝምታ....እንደን ያለ መደበቅ?
እና....ልጥይቅህ እምቢልታ
የአበው....የእምቢኝ እምቢልታ
እንዴት ባለ ስልጣኔ
እንዴት ባለ ስይጣኔ
ድምጽህሞገዱን ገታ
እንዴት ባለ ..መበሻቀጥ
እንዴት ባለ መለማመጥ.....
ልጅህ ከውልደ...ጉንዳን....ከህገ አራዊት-ይማግጥ?
እምቢልታ አንተ እምቢታ
ዝምታ ሆነመቁጠሪያህ
ጠመጠምክ የሸረሪት ድር
መረሳት ሆነ ቅስናህ
መኅብኘት ሆነ ያንተ ግብር።
ልጅህ አቀበት አዳጠው....
ጉልበቱ ለስደት 'ንጂ...ለትግል አልሆንም አለው።
መሰንቆም...ስለ ውበት 'ንጂ መቼ ያወራል ሰለ አበው
ስለ'ዚያ ገመገም አባት
ሞቶ ድምጽህን ስላ'ኖረው
ስላንተ የዘመን እውነት
ከራር ቢከረር ....ሰለጭን

ስለ ዳሌ ነው ስለ ባት።
ነጋሪት....መጎሰም ቀርቶዋል
ልጅህ ልጁን በቁም በልቶዋል።
አውድማው ቀየው ተራቁቶዋል
ታሪክም አርባ ውጥቶለት
እንደማይመጣ ተረስቶዋል።
አንተም በብህትውናህ
.ታወቅህ አሉ በሰው ሃገር
ከባህታዊም ባህት
ሃገርህን ትተህ የሸሸህ
በሸረሪት ድር ተይዘህ
ድምጽ ነኝ ብለህ የዋሸህ።
አንተ ነጋሪት እምቢልታ
አንተ ያበው እንቢታ
እንዴት ባለ ስልጣኔ
ድምጽህ... ሞገዱን...ገታ
የ-እምቢ እምቢልታውን ፈታ
እንዴት?





**፻ ፍ**

ውስጤ አለ
እምቢ ያለ
የማይወጣ.... የማይነጣ
ፍንተው በሎ ላይታይ
የዘለሰኛ አሰቃይ
ጋይ በጋኝ
የማንነት 'ሻይ
ህመም አለኝ
ጣፍ የሚለኝ
በቁም ቁመው ብራና ላይ
ያ ብሶትህ ቀልሞ ይታይ
ሃይ!
...ህመም ዐለኝ
ሲወርድ ሲዋረድ ተዋርሶኝ
እንደ ቡና ቁርስ ተቁዋርሶኝ
ጩኸ የሚለኝ.... ህመም አለኝ።
ተወግቼ ተነድፌ
በደሜ በማንነቴ
ክብር ሃገር ፍቅር ድንበር
በሚሉት ተዋረድ "ቀንበር
"ተሰብሬ"
ተዋርሶት እሱም ካ'ይኔ

ተንሰቀሰቀ ብእሬ
ስጋ አረገዘ ግንባሬ
ተንተገተገ ሚስጥሬ
ሃገር የሚሉትን ምጥ
ድንበር የሚሉትን ምጥ
ወገን የሚሉትን ምጥ
ወ'ግን ላገር ሲሉት...ሸሽቶ
ባንዳነትን ሲቀላውጥ
ይህን ሳምጥ
ሳምጥ ወይ ሳገላብጥ
ተለከፌ
ይኸው ዛሬ
በሰው ሃገር ወገኖቼ ከሚመስሉ
ከተሸለሙ ጠይሞች
ከተሰየሙ ምስሎች
በመልክ እንጂ በኃሳብ እኔን ላይመስሉ ከማሉ
ልጭብጨባ እንጂ ለስቃይ በፈፁም ካልተፈጠሩ
ትዝታኔ በኔ መጨነቅ
ቤት ስመታ ራሰ መነቅነቅ
ግጥም ስወርድ መደነቅ
እንሁን ሲሉ መራቅ
ለትንተና...ተደርቶ ምላስ ቆልፎ መራቀቅ
እና ዛሬ
አዳርሹ ጢም ብሎ ይኸው ከፊታቸው ቆሜ
በወል ቤት...በሰንሳ መገን... ያገሬን ፍቅር ታምሜ
የኢትዮጵያን ፍቅር ታምሜ
ያውም በደረቅ ምድር ያጥናህ የሚል በሌለበት
ህመሙዋ ህመማችን ነው ስቃዩዋ ስቃያችን ነው...
የሚል.... አንድ ላመል በጠፋበት





መሬት መመራት...ካገሩ.... ከክብሩ የበለጠበት
በበዛበት...
እያደራጁ ያጃጁት...
እያደራጁ ሲያፋጁት...
በዝባዝንኬ ተፈቶ...
ባሃገሩ ላይ ፈንድቶ....
የራሱ ደም ለራሱ.... ዞሮ ራሱን ካልገማው..
አከሌ ምን አግብቶት ነው....አቤት ሲባል የሚሰማው፡፡
እና እኔን....ፃፍ ይለኛል....
በአኸያ ዛፎች ላይ.... መሰንቆዬን የሰቀልኩኝ
በባቢሎን ወንዞች ዳር
በኔው ዘመን ያላቀሰኩኝ...
ሃገር አፈር መንደር ያለኝ እያደለ ያለደለኝ
ይገርመኛል...
መገረሜ ጋብ ሳይል ኢንደገና ደሞ ያመኛል
ፃፍ ይለኛል፡፡
ፃፍ አንተ የዋሽራ ሽንት
ያርሲ መለሎ ዝግባ
መጨነቅህም ይጨነቅ ድርሳንህ ከማህደሩ ከሰሚው
መቅደሰ ልብ ይግባ፡፡
ሥፈፍ በየበርሓው
ባሸዋው እንዳ'ፋር ግመል
ፍሰስ በገዳማቱም እንደመቤቱ ጠበል....
ታፈስ እንደጎዣም ማኛ....
ድረስ ከወጣቱ ልብ... መሰመርህ ይውለድ አርበኛ፡፡
ፃፍ....
በብሶት ቤቱ ያደረ...
ማደሪያውን ካውድማው... ሞዜሩንም ተጉዋሮ....
ተጎተራው የቀበረ....

ይነሳ ማልዶ ይገስግስ...
በጥፍሩ አቀበት ይንከስ.....።
ግን አንተ ፃፍ... መክቱብ እሙ- ነፃነት...
ለስቃይህ ማስታገሻ... ለጨለማው መንገድ መብራት።
ፃፍ!
ይውረድ ይዝነብ የስንኝ ዶፍ
ንከር ቀለም
ፋቅ ብራና ያ ጊዜ ደርሶዋልና
ፃፍ!
መክቱብ እሙ-እእላፍ
ይነበብ መስመርህ ይርቀቅ
ከጥቁር ራስ እስከ ለቂቅ
ዲያቆን ካህን መልከ ፄዴቅ
ብርሃን ብርሃን ይልቀቅ።
ከተብ!
ዛሬ የነገሰው ይነሳል ከነመኖሩም ይረሳል!
በል!... ያስገመግማል ማዕበል
ህዝብ ይጠመቃል ከድፍረት... ይጠጣል የጀግና ጠበል።
በላ....
የዘረኝነት አሽከላ
ቃሬር...የደም ሙሳፌር የህዝብ ሬሳ ሲበላ...
ደረሰ ሰው ገስገሰ.... እምቢኝ ወይም ሞት ነገሰ።
ጥራ....
ስንኝህ መለከት ሆኖ....ድርሳነ ትግልን ያውራ...
ጥራ....
ከጋምቤላ ባሌ-ጎባ
ጅሁር ማጀቴ አውራ-አምባ
በል... ሃሙሲትና መተከል
አርማጭሆና አንኮበር





ጋፋት ይፋት ስልጤ ሰላሌ ሰባት ቤት...
ተነስ !
አንተ የጅማ ንጉስ
የጅፋር የክብር ደም ውርስ የገረሱ ዱቄ ውስውስ
ይበቃል ይበቃል ተነስ።
ዘመን ኢነደሸማኔ መወርወሪያ ይፈሳል እንደ-አባይ ዥረት
ቁጭ ብልህ አሳለፍከው...እድሜህን ታርክ ስራበት።
አልሰማህም እንደሁ ትናንት... ገላው ላይ እሳት የጫረው...
የውስጡን ፍም ለማስወጣት... ነፃነቱን ብሎ እኮ ነው።
ታዲያ መቅደላ ምን ዐለ
ሲባል ሃገሬው ምን አለ?...
ሲባል የኔ-ሰው...አካሉን....ለነጻነት አቃጠለ...
ሲባል ጉራጌው ምን አለ...
ሲባል ከንባታው ምን አለ....
ሲባል አኦሮሞው ምን አለ....
ምን አለ አማራው ዛሬ....
ምን አለ...ያ የኔ ትግሬ....
ባሉላ እምነት ያደገው
ሰንደቁ ሃኒሽ እንዲታይ ማፅዋ ላይ እሰቀለው
ከምጽዋ..እስከ....ሃረርጌ.....
በራስ ጉግሳ...በራስ ዳርጌ.....
መቻቻልን የተማረው
ቀኝ ግዛትን...እምቢኝ ያለው.....
ዛሬ...ሃገሬው ምን በላው?
ባክህ ተነስ.... አንተ የክብር ንጉስ
አንተ ውጣት ዠግና አርበኛ...
ሰባት ነበሩ እነሱ...
በምን እንደምን ተሸለው
ለሃያ አመታት ነገሱ...

በላ.... ቀበቶህ..ጥብቁ አይላላ...
አመፀህ ቅጥረኛ ይብላ።
እየገደሉ መሞት ጥንትም ያባትክ ነውና...
ኢትዮጵያዊነት ነው ሰርግህ...
እምቢ በል የኔ አሽወይና።
በል...
ከህዝብ ብሶት የመጣ...
በብረት ጉልበት አይቆምም
ንጉስም በሰራዊቱ ባኟቢዎቹ አይድንም....
አሁንም አይሆንም... በል...
ከወሩ በዚህኛው ቀን ቁራዋም አትመለስም ምድርም
በደንብ ይደርቃል
ኖህም የመርከቢቱን ከለላ ክዳን ያነሳል
ፍጥረትም ባምላክ ትዕዛዝ...ድጋሚ ይርመሰመሳል... በል
አይሆንም... አሁንም....በል...
አይሆንም በብረት ጉልበት አይወሰንም ማንነት....
በላ.... አንተ የዋሽራ ሽንት...
"ምን እጅ አለኝ የሳት ሰደድ አያውቅም ከንዴ
እንደሚያነድ..."
በላ!





## ይህን ን ለ ማ ዎ ት ነ በ ር

አንተ 'ያብረሃም አምላክ የይሁን ትንፋሽ ጉልበቴ
በፍቅርህ ከገነት ሳድር ረቆ ልዩ ፍጥረቴ....
በግን በግ ብዬ ስጠራ....
ውስጠ ባህሪውን ማያ
የዋህነቱን መለያ....
እፍ የተባለው ትንፋሽሕ
ይሁን የተባለው ምጥቀቴ
እሱ ነበረ እውነቴ
እሱ ነበረ እምነቴ
እሱ ነበረ ጉልበቴ....።
ቃሌ የተባለው እውነት
በኔ አድሮ ኪላራ ስውረድ
በማህሌት እና በያሬድ....
በእዝልና ባራራይ
እንደ-እዝራ በመሰንቆ.....በፍቅር ልቤ አንተን ሳይ።
አሃዱ ሳይባል ቆሜ...
ሲነጋ ከደውል በፊት...
በመቅደስህ ቅኔ ስቀኝ
እምባዬ ሲተናነቀኝ....
ተደፍቼ ፍቅር ሳለቅስ
የጨው ውሃ ቅንጤን ሰብሮ....የመሃል እናቴን ሲገምስ።
ሲምሽ ካሞራ ሁዋላ....
ደጀ-ሰላሙ ሲዘጋ

የኔ-ቢጤው በቀን ውሎው
በራብ የተጣበቀ ...
በጠሃይ ምች የደረቀ....
ትናጋውን ሰቦ ሲያዛጋ።
እንደ-ጉግስ ተጫዋች ወገብ
በፍሽጊያ እረፍት ሲያጣ....
እንደርጥብ ማገዶ ጠዞ....አይኑ የቀን ውሎውን
....ቅሪት ብሶቱን ሲያመንጭ....ቅሪት ብሶቱን ሲያወጣ።
የቀን ቅርሞሹን ለማታ...በብጣሽ ፌስታል ውል ሲያሲዝ....
ወደማደሪያው ሲፈታ
አጨናባሪው ተመፅዋች.....
ጉበት የቀባው አካሉን ጭቅቅቱን ውሃ ሲረጭ....
ቀን ለቁራሽ ዳቦ
እጅ እግሩን አስነካክሎ....
ሌሊት በጨለማ ሃይል....ለቅሚያ ልቡ ሰልጥኖ....
ለንጥቂያ ነፍሱ ሰይጥኖ....
ውሃ ባልጠጣበት እጁ.
ሲምሽ አንገት እያነቀ
ብድሩን ደም እየጠጣ.
የብራ ስንኩልነቱን....
በድቅድቅ ሱሱን ሲወጣ።
ድውዩ የተኛበትን
አንዛውና ቁርበቱን....
ጅብ እንደቀማው እረኛ...
ከብት እንደጠፋው ቆለኛ....
በየ አራቱም ማእዘን ...ሽምጥ ሲጋልብ ሲሮጥ።
ፀሃዩዋ እንኩዋን ቀልሳ....
ፊቱዋን ከምድር መልሳ....
በሙብረቅና በጉሙ ግልጥ ገላዋን ተነቅሳ





ለነገው አዲስነቷ የዛሬን ደም-መና ለብሳ
ስትሽፈን
እኔና አንተ ብቻ እኮ ነን
በተዘጋ ደጀ-ሰላም.....የንባ አስራት የተጋባነው....
አባቴ ብዬ ስጠራህ......
"ይህ የምወደው ልጄ ነው" ነበር ያልከው።
ታዲያ ዛሬ...
ከብረሃን ምድር አውጥተህ የሎጥ ምደር ላይ ጣልከ.
ይሁን ብዬ ስቅበልህ....
ፂዮኔን ባሰብኩ ጊዜ....
በንባ ፈንታ ለለበጣ....
ለሚቀነጥጥ ልቦና ለርጉማ ምንነት ሰጠኻኝ።
እየገባህ እያወቅኸው
ነጭ እጣንና ቁርባኑ
ፅናጽልና ደውሉ....
ጥብጠባውና ስግደቱ
በጥር ታቦቱን ከቦ እየሰገዱ ማንጋቱ....
ለንቁጣጣሽ ዋዜማ ...የቼዋጌሚ ሰሞን ጥምቀቱ...
በሩፋኤል እርቃን መሮጥ....
ላዲስ አመት አደይ መቁረጥ....
እያወቅኸውው ትዝታዬን...
እራሴ ላይ በርጩማዬ...
በዠርባዬ የነሃሴን ዶፍ
ከበስተ-ኋላዬ እያቴ ጉልበቱዋ....ለምርኩዝ ሲሰንፍ...
ምዕመኑ ኪላራይሶ...እግዚአ አምላከ ሲወርዱ
እንደጤፍ ዘመመን ታጥፈው ለስምህ ክብር ሲሰግዱ....
መሃል ላይ የልጅ አንጀቴ በፍልሰታ ጦም ሲገረፍ
ለዝከር በተሰበረ..ጥፍጥፍ ቂጣ ጦሜን ስገድፍ።
እያወቅከው....

ደጀ-ሰላም በተመስጦ...
እቤት ስመለስ ለክብርህ...
ግንፍል አሹቅ ወይ-ሽልጦ።
ይሄ ነበር....
ለባዕልና ለክብርህ...የቡሄ ሙልሙል ሲጋገር...
እንደ ትጉህ አራሽ ሞፈር
ሽታው ምራቄን አለስልሶ...ላሃጭ አድርጎ ሲነጥቀኝ....
ጢሱ በእንባ ሲያጠምቀኝ....
በመዳፌ አይኔን ይገፍ....በ-አይበሉባዬ ለሃጩ....
ባቁማዳዬ ሽልማቴን...የቡሄ ሙልሙል ዳቦዬን...
የሆያሆዬ ቀን ምሴን....
ይሄን ነበርኩ።
ዘወረደ....ከዚያም ቅድስት
ምኩራብ መጻጉዕ ደብረ-ዘይት
ገብር-ኄር ና ኒቆዲሞስ
ሆሰዕና ና ለ'ተ ሃሙስ
ሳወድስ ዕርገትህ ሲደርስ
ይሄን ነበርኩ።
ፋሲካ ፍስኩ ደርሶ....
የተላወሴ አንጀቴን...በቅጥቅጥ ጉበት እንዳርስ
ሽንፍላ ገልጬ ሳጥብ...ፍርንባ ቀጥቅጬ ስጥድ...
ወተት አንጀት ስጎነጉን።
ከዶሮ ኩላሊት ጠጠር....ከሆድ እቃዋም ዛጎል....
ከታቃፊ አንዠቱዋ ዕንስዋን...ቅርፊት ያልሰራ እንቁላል።
እንደ-በዝባዥ ፋሺሽት ጦር...ስበዘብዝ ስበረብር....
ለክብርህ የሆነ መስሎኝ አብ እመቴ...
አብ አባቴ....
እቤት አልኩህ።
ህጣን ሆኘ ፊደል ስጭር....





ስምህን በስንጥቡ ጫፍ .....
ስከተልና ስገፋ....
ለኮልታፋው ማላሴ ምስ...የየኔታ እርጥብ ጅራፍ...
አስተካከለህ በለው ሲላኝ....
ጬዋ!!! ብሎ ፍቅር ሲያስጠራኝ....
ግእዝንና ካኤብን....
ሳልሰንና ራብዕን....
ሃምስንና ሳድስን
አበገደ እና መልእክተን...
ዳዊትንና ተግሳፅን....
ብሉይንና ሃዲስን
አንተን እያልኩ አነበብኩኝ፡አነበነብኩ ።
ዛሬ ግን በስደት ምድር....ከንቱ እስኪመስለኝ ጠሎቴ
ስግደቴም የውሸት ነገር
ያቺን ጥቁር አፈር እያሰብኩ....
እንደ ፈራእን ግዞተኛ ለቁና ስንዴ ተሰደድኩ።
እንደ-እዮብ ባልጋዬ ላይ መፈጠሬን ዳግም ረገምኩ....
ብረሳሽ ቀኜ ይርሳኝን ዳዊቴን ሳልደግም አደርኩ።
ያው-ዛሬ እንደምናውቀው....
መቅደስህንም የሞላው...ትጥቁን የጣለ ሽፍታ....ወደ-ገባ
ዘራፊ ነው...
ታቦትህንም ያቆመው የኮንትሮባንድ አቡን ነው።
ይህንን ለማየት ነበር አርባ ኩዳዴ የፆምኩት
ደብርና ደጀ-ሰላም ገዳማትህን የሳምኩት
ጠበልክ ግርጌ ያደርኩት?
ይህንን ለማየት ነበር?
በጣና ገዳም ጋድ ይገፍ.
ግሸን ለማሪያም ገሸኘ.
ደበረ ሊባኖስ-ደ-ብሬ

ወከፈሌ ገብርኤል አከፍዬ
በዲማ ጊዮርጊስ ስም ምዬ
ላስታ ከላሊበላ...አክሱም ከጺዮናዊ ስር
ደብረ-ብርሃን ስላሴ ሀንፀተ-ፋሲል መቅደስ ስር
በጀርባዬ ተንጋልዬ
መልከ ቅብህን ሳማትር
ከትብ-ገድልህን ሳማትብ
ያየሁት ራዕይ
ያየሁት ራ'ይ... ምን ነበር?
የቅዳሴህ ደውል ሲቆም
ዝማሬህ ከበሮ ሲነጥፍ...
ውዳሴህ ምህረት ሲራብ...
የዝማሬህ ከበሮ ውጥር....
እርግብግቢቱ ሲረግብ
ፀሎቴና ምጽዋቴ..ይህንን ለማየት ነበር?
እስቲ ልጠይቅህ ...አቤቱ...
ለማያምኑህም ደግ አምላክ የምህረት ጌታ ነህ እንዴ
አጥርህን ገፍተው ሲጥሉ ዘመን በሰጣቸው ዘዴ?
ዛሬም "አያቁምና አቤቱ ይቅር በላቸው ማራቸው ትላለህ
እንዴ"
ተካታይህን በካራ ሲበልቱ በጎራዴ
እስቲ ልጠይቅህ-አቤቱ....
በዚያች በትንቢት ሃገሬ....
አንዱ ጠኔ አስገድዶት ከገንዳ ላይ ቁራጭ ስጋ ጉንዳን
እራግፎ ሲበላ
ሌላው በቁርጥ ያበጠ...ወይ በትዕቢት የተናጠ..ጋንጃውን
እየዳሰሰ...ሲናገርና ሲያወራ
ስለማያውቀው 'ራሱ... ሰላልተፈጠረበት እሱ.. ..ስለዚያ
እርኩስ መንፈሱ.....ለኔ ለባሪያህ ሲያብራራ





ይህንን ከሆነ ሃገር የተሰፋ ምድር የምትለው
ወይ የምጻት ልጆች ነን
ወይ የእፉኝንት ልጆች ነን
ወይ መኖራችን ውሸት ነው።
እናስ ይህንን እያውቅህ የስቃይ እንባ ሳነባ...
እንደምን ሃገሬ ተውካት ለቀማኛና ለሌባ.....
አንተ አቤቱ!

## ወንድ ማለት

ወንድ ማለት....
ቀና ሲል እሳት
ዝቅ ሲል....ትንታግ
ግንባሩ በትር....እንቢታው ፈለግ።
ወንድ ማለ.
ጠረኑ የዳልጋ
ቁጣው ያንበሳ....
ወንድ ከሆነ....ወንድ
አንዱ ብዙ ነው.....ስየማይረሳ።
ወንድ ማለት.....
ገመገም....ሰብሮ....አቀበት ወጥቶ
ምን ተነካ እሚል....ሃገር አቅንቶ።
ወንድ ማለት
ምልጃ እማይሻ
ከብሩ ኩራቱ....እምቢታው ጋሻ
ጸጥ ሲል ነበር

ሲነጥር.... ንስር....ም የለው ቁጥር
ወንድ ማለት
ከጭን ፈልቅቀው....ትግል ያ-ላኩት....
ስኩዋር አልሰው....አሙዋስነው ያልናቁት።
ወንድ ማለት.....
የማያዳልጥ.....ጽናተ ዳዊት......
ሞቱ ውዳሴ.....ስራው ነው ትንቢት።
ወንድ ማለት.....
ከልጅነቱ ገና ሲወለድ....
በላይ ተብሎ....በላ የሚያወርድ.።
ሹመቱ....ስራው
እምቢታው....ክብሩ...ታሪክ ያሰራው።
ወንድ ማለት
የኮሶ ሻጭ ልጅ.......ልብሱን በእንዶድ አጥቦ ያደገ
ሙቅ ውሃ ለምዶ .....መቼ....ፈገገ
ዝናና ክብር መቼ ፈለገ?...
ያኔ ጥቁር ነው....ጥቁር አንበሳ
ራያን ሆኖ....የሚያጋሳ
ያኔ ጥቁር ነው ጥቁር አንበሳ
ከሸዋ ጎንደር... ከጎጃም...ጅማ...ፈረሱን ገርፎ...ጦሩን ያነሳ።
ያኔ ጥቁር ነው....የጥቁር አሽከር
ግብሩ ድንበሩ
ሰሞኑ....ሞፈር።
ያኔ ጥቁር ነው....የደቡብ ጦና
የዋሽራ...ዝርፍ.... ፍሰት የጣና.።
ያኔ ጥቁር ነው
ምጽዋ ደርሶ....ሰንደቅ ያቆመ.....
ዛሬ ጀግና ነው....ገና ሳይጀምር....ባ-ዐ-ድሜን....ረግጦ
የተደመመ።





ዛሬ ጀግና... ነው....ስለ ሽራሮ የተሙዋገተ.....
ሃሰብን ሰጥቶ....ሸሽቶ የሞተ።
ዛሬ ጀግና ነው....
ጋምቤላ ሲሸጥ....ድምጹን... የሰጠ
ድንጋይ ወርውሮ ተሰፋ የቆረጠ።
ዛሬ ጥቁር.....ነው
ሂድ ሲማሊሞ ብለው ሲገፍት
በግብጽ አሸዋ..የለመለመ
ሸሽቶ በመሞት የተደመመ።
ዛሬ ወንድ ነው....
ወንድ ሆኖ የመጣ....
ውሃ እየገፋ ሮም ለመድረስ ተው ላኩኝ ብሎ....ደርሶ
እሚቆጣ።
ወንድ ግን ማለት.....
ሃገሩን ጥሎ ያልኮበለለ
በየጅረቱ ያልተማማለ።
ወንድ እኮ ማለት....
ወንድ-ም የሚሆን....ወንድ-ም ሲሞት....
ስኩዋር ሲያልሱት...ልቡ የማይሸት....
ቅኔው....ተግባሩ.....ፍርዱ ነው ስራው
ሳያስተምሩት....ታሪኩ የገባው...
....ወንድ ምን ነበር ዛሬ ዘንድሮ....
ሰበበ ብዙ....ልሳነ ሮሮ
ወንድ ምን ነበር....ምን አሉ ትናንት.....
ዜና የሚሆን....በናት ሃገር ሞት።
ወንድ ምን ነበር....እንደምን ያለ
ወንድሙን ገሎ ያስተባበለ።
ወንድ ግን ማለት
"ወንድ የሆነ ነው....ወንድ የጠፋ ለት"።

## የዘንድሮ ውስጠ ወይራ

የህልቆ መሳፍርቱ መብራት...
እንዴት ነህ ጃል አባ ፍርሃት...
ለዘንድሮው ያገሬ ሰው
የሆንከው የመኖር ጉልበት
ታሪኩን ንቆ...ለከርሱ
ውስጡን ደብቆ...ምላሱ
ደስ ብሎኛል እያለ
ባንተ ቅቤ እየታሸ...
ያንተን ቅኔ እንዳ'ቀረሸ....
ውስጡን ንቆ እንደሸሸ...
ቢነጠል ወይ ቢገነጠል
ሆዱ ሞልቶ ውስጡ ሲቃጠል
እንደ አመፀኛ ሰንጋ...
ባንተ አሞሌ ሲ-ባበል...
አዬ ፍርሃት ንጉሱ..
አበው እንዳልዘበቱብህ
ነገስታት ሽጉጥ መዥርጠው
ቃታ ስበው ከደማቸው....
አንተን ገለው መሞታቸው....
ንፁህ ክብራቸውን መርጠው...
እንደዚያ ነበር ያለፉት





የልጅ ልጆቻቸው ዛሬ...
ክብር አምቢታቸውን ሸጡት

እንድምን ነህ ንጉስ ፍርሃት
የሆንከን የተስፋ መብራት
እንድምን ነኽ መኖር ደጉ
"ብልህነት ሆኑዋል ዛሬ..."
እድሜ መቁጠር እየሰጉ።
ውጉም ተሻሽሎ ባንተ.....
"ማ-ለ-ማ-ይሞታል ዝ'ምበል"
እድሜ ላንተ. ይኸው ዛሬ....የሃገር ትል...
የዘመን ቅማል እንቅመል።
አዬ ፍርሀት ጠቢቡ...
እንደ ሴተኛ አዳሪ አልጋ
ልጆችህ እምቢኝ! ረገቡ።
ፍርሃት ተሳክቶልሃል...ይህው ዛሬ ባንተ ጉልበት
መቅረዝ ሆነህን ለፅልመት...
ለክህደት ፋና መብራት...
ተከንብለን ባንተ መከሊት...
እየተጉዋዝን የኋሊት
አንተን ጎርሰን
አንተን ለብሰን
ባንተው ፈሳሽ ተሙለጭልጨን
የተፈንጋይ ፈንጋይ ሆነን
ራሳችን ላይ ተቀጥረን
እግዚኦ በ-አንተ ላንተ-
ያንተን እድሜ እንቆጥራለን።
ፍርሃት ...ላንተ እንቁጣጣሽ...
ለዘመኔ ሃሞት አፍሳሽ....

አደይ ላንተ...ሰርዶ ላንተ
አይንህን ባይንህ ስላየህ።
እንቁጣጣሽ አደይ ላንተ
ከዘመን ዘምን ተሻገርክ....
ጭንቅላት ለሆድ ተገዝቶ
አንተ በአንደበት ተሰብክ....
ከፍረሃትም ፍርሃት...
ሲቆጡት ገና የሚሞት....
ሲገልቡት ቂጡን የሚሰጥ...
ጉልበቱን በስክስታ የዋጠ...
በቁርጥ ቂጡ ያበጠ...
"ጥራኝ ዱሩን" ...ቀድሞ ያጠጠ...
ከማዕድ-ቤት እጁን የሰጠ
ልቡ በኩርፊያ...የለፋ....
ዘራፍ ሲሉት የሚከፋ....
ዝረፍ ሲሉት የሚያካፋ
ሃገር ሲሉት የሚጠፋ...
በእርዳታ የዱቄት ወተት...የደም ሰሩ የተንፋ....
በቁሙም የንቀት አረም...በቅሎበት ያደርጋል ተሰፋ።
እና ፍርሃት ዘና በል...
ላትነቀነቅ ፀንተሃል...
ጠቢቡ እንኳዋ...ተጠቦ...
እርቅ እያለ ይሰብክሃል።
እሱስ ምን ተለይቶ...
'የውቀቱ ኬላ...ቢላላ...'
ውስጡ ...ባንተ...ተሰርሰሮ...
ምስጥህ መስጠት ቢበላ...
የዕርቅ ቡና ሲቆላ
ገፅ ገላጠ እንጂ ወረቀት...





አነበበ እንጂ መች ኖረ
ለነገሩማ ተረቱም
"ከዲግሪ ድግር ይሻላል"
ብለዋል ሞፊር ያበቱ
እነሱ ኖረው ሞተዋል
እሳት እንደጨበጡ
እንኩዋን በቁም በነፍሳቸው
ሞተውም እንደተቆጡ።
እና ፍርሃት አደይ ይኸው ...ቁጠማ ላንተ ይቀንጠፍ
ፍጥረት-ባንተ ከፉ ሴራ
የእምቢታ ቅስሙ ሲታጠፍ
በቃ ፍርሃት ዘና በል...
ላትነቃነቅ ፀንተሃል....
አከሌ እንኩዋ ተረቶ....
በፍቅር ስም ይሰብክሃል።

## የት ሊደርስ ዛሬ ሃቅ ቢቀለበስ

ሳግ ከጥጉ...ከ ህይወቴ
አንተን ካየበት እውነቴ
ከፍቅር ጥጌ ሲታከክ
ቡዋለተኛ ና ነገረኛ...
ግፉን ባንተ ላይ ሲያላክክ
ብዕርከ ብርሀ ያስያዘው
ጥበብህ እረፍት የነሳው
ሞትህ መሞት መስሎት ሞኙ
ትከሻውን በከበሮ....አሸንዳ ከቦ አስነሳው
አሸንዳ አሸንዳ እያለ።
የስንኝህን ቁመቱን...
የድርሳንህን ውበቱን...
"ብዕር አይሞትም ስትል"
ባለቅኔ መተካቱን...
"ቢራቢሮ ካበባው ላይ"
አንተ በመስከረም አደይ....
እኔ ደሞ ባንተ ፀደይ...
ስንዋሰብ ራዕይ ለ-ራእይ....
ዛሬን መተንፈስ ባትችል...
ከአፈር በላይ...በአካል...
ሂደት ዝግመትህ ባይታይ....
ድርሳንህ አይዳፈንም....
አይፋቅም ከታሪክ ላይ።
እናም ላንተ የምፅፈው...
በብእሬ የምነድፈው....





ካንተ የጠጣሁትን...
ባንተ እኔ የሆንኩትን...
ይቺን የፍቅር ግርሻ....
አሳንሰከ አትይብኝ....
ትሁን ላንተ ማስታወሻ።
የፍቅር ሰዋ-ሰዌ ነህ
ነጻነት ሲያምረኝ የማይህ
መድብል ስገልጥ የማስብህ
ገና በልጅነቴ....
የገለፅኩህ የቅኔ...ምት
የሃገሬን ድንቅ ልሳን...ያስተማርከኝ...ክትብ ውበት።
መስታወት ነህ...ለሂደቴ...
መከሬ ነህ ነብስ-አባቴ...የኢትዮጵያዊነት ኩነቴ።
እስኪ አንተ ዋ! አድዋ በል...
እኔ እንኩዋ ቂም ቢጤ አለብኝ....
አድዋ ብዬ ስጀምር...
የሆነ ነገር የሚያመኝ
የአንደኛው አድዋ ክብር....የሞት ነጻነት ሲያኮራኝ
የሌላኛውአድዋ ስቃይ...ህሊናዬን እያደማኝ
እኔ እንኩዋ ቂም ቢጤ አለብኝ....
አደዋ "ካድዋ" ወዲህ...
እያለኝ ይሄ ብዕሬ...
ግማሽ ባንተ ብዕር ጥልቀት...
ግማሽ በቂም ተሰብሬ።
ስለ-መርካቶ ላውራ ስል....
መርካቶማ በዘመኑ...
ቅርጫቱ በንቁላል ሞልቶ
ዶሮው ዝቅዝቁን...ቁዋ-ቁዋ-ሲል....
በትንፋሽና በግፊያ...አየሩ በጢስ ተሞልቶ....

ያኔ በደግ ዘመን ያኔ በጥሩ ግዜ...
ጥሩ ሰንኘ ወርዶለታል....
አሁን መርካቶ የት አለ...ሰሜን ጭነው ወስደውታል።
ይለኛል ይሄ ስሜቴ።
ጅግናን ላነሳ መውድስ...
ብጠራ የፈደል ጠበል...
ባዘጋጅ የቅኔ ድግስ....
ቃላት ብቻ ነህ ይቅርብህ...
እሱ የፃፈው ለጴጥሮስ...
ያንተ ዘመን...ድንጋይ ቀራጭ...
ዲያቢሎስ ወ-አባ-ጳውሎስ
ይለኛል ይሄ ስሜቴ።
ከጫፍ ጫፍ ሀገር ልጠራ
"አፋር ነህ መሰሎ ብሌን"...
"ሲዳማው ሲዳ ሃማ-ልል"
ልደረድር ያንን ዘሬን...
እንዴት ይሻለኛል ዛሬ...
ማንነትም ታሪክ ሆኖ...እኔም አንገቴን ሰብሬ።
መምከንና መብከንከኑ....
በስንኘህ መባነኑ....
ከዚያ ከጥበብ ጎተራ...
ወል ሰንኝ መገን ብጠራ...
ቀለም ቆጠራው
ድብተራው....
በሰም ቤት የወርቅም ትብታብ
ሲተበተብ የቃል ህብር
ሲተበተብ አሸንክታብ
"ካ-ሲል ስትል"
እግዜር ስልህ-





"ካ-አፍሪካ-"
የአፋር አምላክ....ከአፈር...
ከአፈር የመጣን ቀመር....
"ወረ-ባቦ
ወረ-ይመኑ
ወረ ይሉ"....
ወል-ቂጤ..ቢሉት
ወል-ቃይት-
እትዮጵያዊንት ነው-ቅሉ....
ስትል...በብዕርህ ጉልበት....
እኔ ደሞ ባንተ እውነት...
ሲተበተብ የኔ ህይወት...
እንደበርሃ ግመል...
ለህይወት ጉዞ...ከምኘጭህ...ከብዕርህ ጠል ስጠጣ...
ካንተ የቃረምኩትን---እኔን ተመስሎ በኔ---ስላንተ---በኔ
ሲወጣ....
"የት ሊደርሰ...ዛሬ ስትል"
ሃቅ ተቀልብሶ...ኑሮ...
የዳኝነት ፈረስ ታስሮ...."
ንገረኝ ስለ-ዘመኑ....
አመጣጤን ተርከልኝ....
ሴምና ያፌትም ይፈቱ...ኩሽነቴን...አርቅቅልኝ....
"ጠዋት ፓርቲ...አድሮ ፋልቲ
ሲነጋጋ አርቲ ቡርቲ"....
ዛሬ ልምንድን ነው ማትል....
ዛሬ ለምንደን ነው "አድዋ....
ያለት ምሰሶ አድማስ ጥጉዋ...."
"ሰማይ ጠቀስ ጭጋግ ዳስዋ"....
የሆነችው መሸመቂያ...

የታሪክ ውርደት ማመቂያ...
...የኢትዮጵያዊነት መጥለቂያ....
ለምንድን ነው የማትጠይቅ...
"አዬ ምነው እመ ብርሃን...
ኢትዮጵያን ጨከንሽባት
ምነው ቀኝሽን ረሳሻት...."
ለምንድን ነው የማትላት...
አንተም በተራህ...ዝም አልካት...?
አፈሩዋን በልተህ ለፍቅሩዋ...
አፈሩዋን ለብሰህ ለክብሩዋ....
ዛሬም እስቲ በል "ዋ-አድዋ!"
አደይ ከመቃብርክ ላይ...ፈንድቶ...እዮሃ  ፀጋዬ ይበል...
ገድልህ ሮሆቮት ሁኖ...ያፍልቅ... ጀግና እንደ...ጠበል...
እና እባክክ ዝም አትበል....
ዝም አትበል....በል  እንጂ "እንጃ ለኛ..."
"ለነካሊሽ-ንኩቭኛ" ለከላሽ ነካሽ ደመኛ።
ዝም አትበል በል ነገረኝ...
ወገቤን ልታጠቅ ልቁም...
ያን ቅኔህን አስተምረኝ....
"ብልህነት እንጂ ብልጠት አከትምለታልም በለኝ..."
"ኢንጂ ከበሮ ብንደልቅ"
"አይነጥፍም ያባቶች ጽዋ"
ነጻነት በምንዛሪ...አይሸጥምና ክብሩዋ....
በልኝ
"እየሱስና መሐመድ በመለኮት ቃል ተዓምር
እንደገና ተመልሰው ቢገናኙ በዚች ምድር
ይተቃቀፉ ነበር በቅድስናቸው ክብር
በስማቸው የሚያቦካው ተብታቢው ሁሉ እስከሚያፍር"
በለኝ ተብታቢው ሁሉ እስኪበላ





ዋ! አድዋ ዋ! አባቴ አንተ....ዋ! እኔ ልጅህ
ቃል የምነት እዳ ሆኖብህ እፍ ብለህ ተነፈስከው
በጽናትህ ይኸው ዛሬ አንድ ነብሴን አቅፈህ ያዝከው።
አንድ እምነቴን አከረምከው....
አንድም ከመከራ መዝገብ
አንድም ከፊደል ጥበብ
አንድም ሃ ብዬ አንተኑ
አንድም ዋ ብዬ እኔኑ
ካንተው የወረስኩት ነው
እኔን መስሎ ዛሬ የወጣ
ተው ሲሉት እምቢኝ አባቴን አለሜን ብሎ የመጣ
የብዕር ባልቻ አባነፍሶን ገብርዬን ብሎ  የመጣ
ጸጋዬን ብሎ የወጣ።

( ለባለቅኔው አባት አለም  ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህ

## የመከራ ዙፋን

እንደዚህ ነው...

ወጣትነ... ዛሬም ኢትዮጵያዊነት
እንደዚያ ነው...
የተተለተለ ሱሪ
መከራ የቀመሰ ገፅ
በሰው ምህረት ኑዋሪ...
ያላፊ አግዳሚው ተመፅዋች
የሲጋራ ተጠዋሪ
እንደዚያ ነች።

የጎዳና ላይ ነጋሽ
የመከራ ዙፋን ወራሽ
በወደቀ ቁሩ ግማጅ
ነፍሱዋን ያቆመች ውላጅ
የልቡዋን እሳት ባፍዋ...የነከሰች ምጥ አስወርጅ
እንደዚያ ነች።
እናም አይኖቼ እሱዋን አዩ
በኃሳብ ምትሃት ተመታሁ
ምንነቴን አደበዩት።
ወገን ድንበር ሃገር ታሪክ
በሄደበት እጅ ሲሰጥ
ለውጣ ውረድ ሲማረክ
በየስርጡ ቁሩ ሲለቅም
የባዕድ ዲናር ሲሳለም
ማ!ን አየው ይህን ከፋቱን





ለፅልመት መብራት ማብራቱን...
ማን አየው...
ብቻ ከዚኛው መንደር....
ልብ ፀሎት ሲደረድር...
አግባኝ! አግባኝ! ከዚያ ሰፈር....
ከነጭ ጋ! ተሰልፌ...
እኔም ምላሴን ቆልፌ...
በጎዳናቸው ሰፍፌ....
ለዘመዶቼም ተርፌ....
እባክህ አድርሰኝና....ለመቅደስከ ባላበባ
ሲጋጃ ምንጣፍ ላስገባ።
ፀሎቶ- ዎ -ለገሃነም
ይትባረከ እመ አማሪካ
አምላከ ዶላር
አምላከ ዲቭይ ወ-ስኮላር
በ-ሐውርት -ወ-በየብስ-ወ-በአየር
በኩሉ ምህዋር
ለአለም አለም።
ግና የኔ ሃሳብ ዙፋን ነች
በጎዳና የነገሰች
የዞፈነች: የዘፈነች
ባይኑዋ የምፅዋት ባቲን
የተቸሩኝ ተዘከሩኝ እንቺ-ሆዬን የተቀኘች።
ግና የኔ ሃሳብ እርሱ'ዋ ነች
ፀጥ ባለ የባዕድ ቀዬ ቁሩ ስትለቅም ያደረች
አምሳያ ምትከ የሌላት
ለመቃጠል የፈጠራት
ሌጊዮን መብራት አብርቶ
ለስይጣኔው የጠራት

በስልጣኔው የገራት።
ግን አንዳንዴ አንዳንዴ የምንይልክ ደምየቴዎድሮስ ታሪክ
በውስጧ
በደም ስር ስሯ ሲታደም
በጥቁር ገፁዋ ሲደመም...
አንዳንዴ አንዳንዴ ብቻ
ለማንነቱዋ አፍ መፍቻ
እንድሁ ሲዋሰብ ስሜቱዋ
ሲከለባበስ ግጭቱዋ
ከንፈሩዋ እሳት ሲጠግብ
ያ! ደሟማንነት ሲራብ
አንዳንዴ አንዳንዴ ብቻ
እንዲህ እምትል ይመስለኛል....
"ሃበሻ ነኝ ያበሻ ልጅ"
የቅኔ የጥበብ ጥማጅ
የዘለስኛ ጉባኤ
የያሬድ የ-ዕዝራ ግማጅ
ሃባሻ ነኝ ኢትዮጵያዊት
ስደት ባ'ጢያት ያጠበኝ
የሱስ የዕፅ መቅደላዊት።
ሀበሻ ነኝ ሸማ ሰሪ
የነደፍኩት የፈተልኩት....
እሳት ሆኖ ደሜን ዙዋሪ
ያም ሆኖ ለኔ ዙፋን ነች
የህይውትን የርግማን ምጥ
የሽንት ውሃ የረጠበች....
በጋዝ ም-ገት የቆረበች።
ግን...
አንዳንዴ አንዳንዴ ብቻ





ታርኩዋ ሚዛን ሲደፋ
ስብዕናዋ ሲገፋ
ሰንደቋ...ሸው ሲልባት
ጀግንነት ሲያገረሽባት
ማንነቱዋ የማንነት
ሲቆም ይባቤ ማህሌት
እንዲህ የምትል ይመስልኛል...
ከአፌ በወጣ የፀሎት መርዝ
የተሸከምኩትን መዘዝ...
ምናለ ይበቃል በሎኝ...
ሀገሬም ችጉሩ በቅቷት...
ምናለ ጤዛዋን ልሰን...
ከመከራ ብናወጣት?
እንዲህ የምትል ይመስልኛል።
ያም ሆኖ ዛሬ ዙፋን ነች....
ለመከራ የነገሰች...
በወደቀ ቁሩ ግማጅ....
ነብሱዋን ያቆመች ውላጅ
የልቡዋን እሳት ባፍዋ የነከሰች ምጥ አስወራጅ
ጸጥ ባለ የባእድ ቀዬ ቁሩ ስትለቅም ያደረች
አንዠቱዋን እስራ የኖረች
ያንዠቱዋን ያልተናገርች...የዞፈነች የዘፈነች።

መታሰቢያነቱ  በአማሪካ ጎዳናዎች ላይ የአደንዛዥ እፅ ምርኮኞች ሆነው ለቀሩና  ለቁሩ ሲጋራ ለሚውተረተሩት የሃገሬ ወጣቶች። (መነሻ ሃሳብ ግዛቸው ገ/እግዚአብሄር ደግፌ (" ለገሃነም ጸሎት"መጽሃፍ )

## ተረት ተረት

ተረት ልንገርሽ ህይወቴ
አንቺ አድምጪኝ በሞቴ
ተረት ቢሉሽ ተረት ተረት
አዲሱን ኢትዮጵያዊነት
እየጠፉ አልሁ ማለት
ተረት ትረት።
ጥንትማ ሲተረትና ሲነገር...
ነገር ነገር
ወጣ ወጣ
ወጣ መንዘር
ማን የማን ዘር...
መንዘር መንዘር
የዘር ማንዘር።
ቴዎድሮስ ምን ይልከን ቢወልድ
አሉላ ደሞ...አብርሃምን...
ጀፋር ገረሱ-ዱቄን....
ሳህለ-ስላሴ ዳርጌን።
እንዲህ ነበር
በኛ ዘመን የቆሙብሽ
የነወሩብሽ ኑዋሪዎች
ያነቶቻቸው ጭንቅ ሆነው....
ሞት አምጠው....
ሞት ፀንሰው...
ካሳማ የተዳቀለ...ነጭ ታርክ ይነግሩናል





አመተ አለምሽን ከደው
አመተ ምህረትሽን ሽጠው
ቀጣፊ...አድሜ ይቆጥሩልናል።
አረ-ኢንዲያውም እንደነሱ
እንድጌቶቻቸው ምጥቀት
እንደጋላቢዎቻቸው ርቀት
እኛ እንደውም ጦጣ ነበርን...
እያደርን እንደጠላ
እየፈላን እየጠራን
የዛሬን ሰዎች መሰልን
ያልታደልን።
እና ተረት ልንገርሽ ህይወቴ
አንቺ አድምጪኝ በሞቴ
ተረት ቢሉሽ ተረት ተረት
አዲሱን ኢትዮጵያዊነት
እየጠፉ.... አልሁ ማለት
እየጠፉ ....ያልፋል ማለት
ተረት ትረት።
ወንድም ወንድሙን ገድሎ
"አዛኝ ቅቤ አንጉዋች አስመሳይ"
ሃውልት አቁዋሚ ስእል ሳይ
ቴዎድሮስን ዘካሪ አስታዋሽ
የበላይን ዝከር ነቃሽ
በበላይ ስም መርዝ ጠንሳሽ።
በጠራራ እየገደሉ
ሃገር ቆርሶ እየገበሩ....
ሃውልት አስመላሽ ተጠሪ
"አጭበርባሪ ተቆርቋሪ"።
ያ-የገደሉት ትልቅ አውሬ...

ኢምፔሪያሊዝም ይውደም ሲል....
የሱ ሰይጣን በንሱ አድሮ
ብሎም የነሱን ተፈጥሮ ባህሪያቸውን  ጨምሮ....
ይኸው ዛሬ እንደምናቀው
በዘረኝነት ተጠምቀው....
ጊዜ በሚጥለው ትዕቢት
በመሰሪነትም ልቀው
ይነግሩናል ተረት ተረት
በሚከረፋ አንደበት።
እና ተረት ልንገርሽ
እኔም ዛሬ ባህር ማዶ ቁጭ ብዬ
በቀን ሁለቴ ብታጠበ....
በቀን ሶስቴ ብበላም....
ገላ-ፈራሽ አካሌን እንጂ....መቼ መንፈሴን አጠራሁ
ድርድር ድርብር መንደሩ....
መቼ ትዛታዬን ገራው?
ጠረንሽ እንደናፈቀኝ
የብሶት እንባ እንዳነቀኝ...
በጣት የተገፋ ጉርብጥ ቂጣ ባይኔ እንደዞረብኝ
ላሜ ቦራና ሴደር...
ጭብጦና እስር ቀንበር....
ወገን ላይዳ....መንሽ ጊደር....
ውል እንዳለኝ...ውል አጥቼ....
ከቄየውና ከሽታሽ....
እራሱን በሳተ አሽከር ....
የግፍ ግዞት ተገፍቼ...
ካትላንቲኮ ማዶ ሆኜ ትዝታሽን አነባለሁ....
እኔም ተረት ተማርኩና
"እስኪያልፍ ያለፋል ብያለሁ።"





ውሎ ሲያደር
ተሰፋ ቢስ አማኝ ሆንኩና
"እሱ-ያመጣውን...ምስለኔ"
ታጥቦ በደረቀ ወኔ....
ወርቅን በነጥፈ ቅኔ....
ፅድቅን በሆነ ኩነኔ....
በሽታሽ ላይ በምነትሽ ላይ
በምነት በታሪክሽ ጉዳይ
በመስሎ ኑዋሪነት አድር ባይ
ባጭበርባሪነት ወላዋይ
የታጠብኩት ውሃ አጥምቆኝ
ያጠመቀኝ ውሃ ሙቆኝ
በታሽገ ምግብ ማተብ
አዲስ ባንዳነት ያምጣል...
የዛሬው ኢትዮጵያዊነት።
እና የተረቴ ቅሉ
አምላክ ፍቃዱን ለማደርስ
ባምሳሉ የፈጠረውን
አዳም ብሎ በትንፋሹ በይሁንታው ሲቀሰቅስ
የተሰጠውን ግብር
እንሰሳ መሰየም ተግባር...
ስራውን እንዳያቋርጥ...
እንሰሳ መሆን የማምጥ...
እንሰሳ መሆን የምመርጥ
ስም ያልወጣልኝ አታላይ
ወኔ ያልፈጠረብኝ አድር ባይ...
ይሁን ይሁን እበላ ባይ....
እሱን ሆኜ..ሆኜ ቀረሁ።
ቢረግጡኝ እንደ-ስልቻ...

እብቅ ትንፋሽ....
መቻል መቻል መቻል መቻል መቻል ብቻ!!!!
እሱን ሆኜ...
ሆኜ ቀረሁ....
በተረትና ምሳሌ
መለኪያ በጋጬ ገድሌ
ጠርሙስ በጨበጤ ወኔ....
የነጻነትሽን ክብር...እልኮል ማወራረጂያ አድርጌው...
ያሼሼ ነጋሪት ብጎስም
ፍትፍት እልጫ ብጎርስም...
እውነትና ያንቺ ንጋት
ስካሬን ሳልጨርስ ጠርቶ
እልድን ነገር ተጠናውቶን...
ወይ አያቀስኝ ቅስና...አድርባይነቴ እንኩዋ ጠልቶኝ....
ባናት እንደዞረ የዛር ጦስ
ከፓርቲ ፓርቲ ስቸለስ
ስቅለሰልስ ስቀለብስ
ዛሬም አልሁ
ያለቆቼን አንጀት ሳርስ
የሰሜን እርግማን ሳርስ ዛሬም አልሁ።
እና ለንገርሽ ህይወቴ.....አንቺ አድምጪኝ
ተረት ቢሉሽ ተረት ተረት
አዲሱን ኢትዮጵያዊነት
እየጠፉ አለሁ ማለት
እየጠፉ ያልፋል ማለት
ተረት ተረት
ተረት ትረት።





## የኔ ጥያቄ ይህን ነው

አባይ አ-ባይ....
አንተ ፈሳሽ ተንዶልዷይ
ያፈር ስንቅ አቀባይ
አንተ የግብጥ አድር ባይ
በቁምህ ራስህን ታይ
አይ!
ሊያውም የሰለጠነ....የደበተረ አታላይ
አባይ አ-ባይ።
ማንነትህ ውስጡ ፈሶ
በባህሪ አንተን ለብሶ
ስራክ ከስራው ተዋርሶ....
የትናንት የቅማል አሽከር....ዛሬ ራስ ሆኖ ነግሶ....
ያኘዋከን የወርቅ ጉድጉዋድ
የለገ-ደምቢን እምቅ ምጥ በደም እጁ እያፈሰ...
እሱም እንዳንተ ረከሰ
እሱም እንዳንተ ፈሰሰ...።
አባይ ነው በየበርሃው...በየስርጡ የሚስረቀረቅ
መፈጠሪያውን ሸርሽሮ በውሃ ፈረስ የሚስቅ።
አባይ ነው ያ አታላይ....
ለግብጥ የውሃን እሰይ የሚቸር የደለል ሲሳይ
ሸንጡ ዳሌው ተረከዙ....ለምስር ማዝተ የሚጋይ።
አባይ ነው ያ-ጉራማይሌ....መሰደድ አሸዋ
ሆኖት...የሚሰረግ እንደ-ሸበሌ።
ታዲያ እሱም አንተን መስሎ
አህያ ታህያ ውሎ
ፈሰሰ አንተን መሰለ
ሃገር መንደር አማሰለ...

ቅርስ ድርሳን እየጣለ...
ታሪክ እያቃጠለ።
ይኸው ዛሬ የነገሰው...
እጁን በንፁሃን ደም...በህዝብ አጥንት የነቀሰው....
በስራ አንተን መሰለ....
ከግብርክ ግብሩ ተቀዳ...ተጠመቀ ካንተ ጉ-ዋ-ዳ።
ያ-የጎተም ገበሬ እንኩዋ....
እስርህ ተፈጥሮ የኖረ...
ቤቱን ስትደረምስ....
መሬቱን ገፍተህ ስትቆርስ...
መቼ ካንተ ከሀደት ሃገር ማፍረስን ተማረ....
በላይን ወለደ እንጂ....
እምቢኝ የቴዎድሮስ ቅጂ።
መቼ-ልቡ አንተን ሽቶ...ለክህደት ተራገበ....
መቼስ ሃገሩን ለሽያጭ ለጨረታ አቀረበ።
መች ባህሪህን ወረሰ...
ግፋ ቢል ሆዱን ተባሰ....
አባይ ነው አ-ባይ አታላይ
የቀዬ የመንደር ስቃይ
አለ እንጂ መች ተከትሎ....ጥላህን ይዞ ፈሰሰ?...
ግፋ ቢል ይህንን እርግማን...
ትዝብት ውረስ የብሶት ቃል ለልጅ ልጁ አዋረሰ።
ታዲያ እንዚህ ከየት መጡ...
ወይ ከጅረትህ አልጠጡ...
ወይ-የማሽላ ዛላ ውይ የበቆሎ አገዳ ባንተ መከር
አልቆረጡ...
የምጣዶቹ እያሉ እንዴት እንሱ ተንጣጡ...
ይህንን ዘላን ባህሪ ከወዴት የዘውት መጡ...?
እንዴት ጎተሚው እያለ መረቦች ባንተ ልክ ወጡ?...





ያ-ገው ገበሬ ሳይመስልህ
ከብቶቹ በጅረትህ ሽንጥ...በውሃ ጥማት ሲነዱ
እንቦሳውና ጊደሩ ከፍሰትህ ጎን ሲ-ነዱ
ከባህሪህም ባህሪ
ከመልከህም መልክ ሳይገዱ
እንዴት ያድዋ ልጆች በግበር ካንተ ተቀዱ?
አድዋንማ ስናቀው
ክብር ነበረ ለናቀው...
ባጥንቱ ስሙን ለጣፈ....
በሞቱ ድል ላረቀቀው.....
ያባርነት ግባ ካፈር
በዘመን አ-ባይ አባዮች...የማይገሰስ ክብር
"ለነጣነት የሞት ጥዋ...."
የተጎነጨት ትንሳኤ...የድል እርገት ነው አድዋ!!!!
አድዋንማ ስናቀው
ክብር ነበረ ለናቀው!!!
ሰንፔር ነው የአፍሪቃ ፈርጥ...
ከምስራቅ የወጣ ጸሃይ...
ስጋጃ የጎህ ሰንበሌጥ።
የኔ ጥያቄ ይህን ነው
ታዲያ እንዚህ ከየት መጡ?
ትናንት በፍቅር ትኩሳት..
ዛሬ በጥላቻ እሳት
በፈጠሩት እሳት መሳት...
ባጉል ጥላቻ ታጅለው...
የመረብ ወንዝን ጀንነው....
አይደለም እንዴ...አጅበው...
መድፍ ደቅነው የሚያድሩት?...
አንድ ቢኖራት እሱንም በዘነዛ እንዳሉት?

ታዲያ አንተ በማን ተዋርሰህ
ማ..ቢወልድ ማ ተዳርሰህ...
ባ-ህሪህ ለመረብ ሰዎች
ሲሳይ ሆኖ እንደ-ግብጦች...
ተንዶልዱሎ የፈሰሰ...
ተንከባሎ የደረሰ?
የተኛው አጥንት ተቆጥሮ..አክሱም ጺዮን ያነገሰከ...
ሸሬ እንዳ-ስላሴው...እንዴት ከብርሀን ወረሰ?
መሳቅህ ያው ማሽካካትህ
አፈር ጭነህ መዘርጋትህ
ጥንትም የተፈጥሮ ነውና
አ-ባይ አባይ ማንነትህ
አልደነቀንም ተጉህ
ተዘር-ግተህ መግዛትህ።
የኔ ጥያቄ ይህን ነው
ከምንጭህ ወዝ ያልጠገቡ
ከፈሳሽህ ያ'ረጠቡ
ከደለልህ ወይራና ሙዝ...
ለውዝና ሙዝ ያለቀሙ
እንዴት አንተን ተመሰለው...
በተግባር አንተን ቀደሙ
በግብር አንተን ደረቡ?
እንዴት 'ነሱ ፈሰሱ
በየትኛው ዝምድናቸው ...ከ-ጦቢያ... ላረቢያ...
መሬት ሊሸጡ ተነሱ?
አነተ ለፈራኦን ልጅ አፈር ጭነህ ስትገባ
አምሳያ ወንድ ልጅ ወልድከ...የመቅኒ ደም የሚጠባ...
ሃገሩን ለህንድ የሚሸጥ...አፈሩን የሚያስማማ።
ጉድ ሳይሰማ ይላሉ





ጉድ ሆነን ሃያ መስከረም...ሃያ እንቁጣጣሽ ጠባ....
አባይ በሰው ተመስሎ....ድንበር ስለት እያስገባ።
ያም ሆኖ የኔ ጥያቄ ይህን ይመስላል ባጭሩ...
ሃገሬው ለመፀዳጃ....ድንጋይ ለመለቅለቂያ...
ለግብር ውሃ እያነሱ...
"በተለመነ እህል ህዝባቸውን እያስፈሱ..."
ወርቅ ነን አንተ ጨርቅ ነህ የሚል የዘመን አ-ባይ...
አባይ ጀረቶች ተንሱ....
ሃገር መንደሩን ሊቆርሱ
ቀዬ መንደሩን ሊያፈርሱ...
የመረብ ልጆች ለግብርህ....ለህልውናህ ፅናት...
ብልጣብልጥ የልሳን ከፋት...
ከከፋትም ያንተን ከፋት
ሃገር መቁረስ አፈር መግፋት...
ቢዚህ ሰልጥነው ተነሱ።
ምን አይነት የግዜ እርግማን አውራሽ አበው ነው የቸረኝ...
ብዬ ባንተ አልቅሼ ...እንሼ እንብቼ ሳልጨርስ
እንደ-ሽማኔ መወርወሪያ የፈጠነው ጊዜ ደርሶ
እርግማኔን ውርጅበኜን...ሳላቁዋርጥ የኔን ለቅሶ...
ያ! የትናንት ጩቅላ...
ባንድ-ባሰር አመት የቀደምኩት
ግራና ቀኝ ተመልከቼ....
ገባርህን ያሻገርኩት
ስትናጥ አፈር ስትልጥ
የተሸከምከውን ሲሳይ...ለመገላገል ስታምጥ
ቀና ሳይል መሄድ ሳይችል...
በሁለት አ-ባይ ወጥሬ...
በሁለት አባይ ጠፍሬ እንገት መድፋት ያስተማርኩት
እሱም ዛሬ ደረሰና

ጠየቀኝ አወቀኝ ናቀኝ
ጠየቀኝ አወቀኝ ናቀኝ...
አንጻራዊነት አለ እንዴ ባንተ መንደር ግራና ቀኝ?...
ጠየቀኝ አወቅ ናቀኝ
በዚህ ባንተ ቀዬ...
የኔ በምትለው ሃገር....
ፈሳሹም ንጉሱም አ-ባይ
አይደለም እንዴ ቅጥረኛ....
የፈረሰኛ አታላይ?
የሱ ጥያቄ እሱ ነው።
የኔ ጥያቄ ይህን ነው...
ምናልባት የልመና ቃል ..የሃሳብ ግሸበት የምለው...
ምን-ነበረ እንደ ጥንቱ ዮርዳኖስና ኤፍራታን ግዮንን ሆነህ
እንደጠበል
ከጅረትህ ሳር ቄጤማ...ምናለ ሰርዶ ብንነቅል?...
ማናለበት ጊደሮችህ ለግብጥ አረብ ከሚሸጡ...
ምን አለበት ከሽንጥህ ጎን ትኩስ ምንጭህን ቢጠጡ
ምን አልበት መርገብህን መንሳፈፍህን ቢመጡ...
ምን አለበት?...
ምን አለበት ሰርዶ ሆንህ...ለግጦሽ መስከህ ቢወጡ?
ምን አለበት?
ለመናዬ ላንተ ሩቅ ነው....
እትብትህን ጣና ቀብረህ....ሞትህ ከሰው ሃገር ነው...
ለመናዬ ላንተ ሩቅ ነው
በሰላሳ አመት በርሃ...
አምሳያ ያገኘህ ውሃ....
ላዛፍ እንከዋ የማትሆን....
ለሸእንበቆና ቀርከሃ።
ፈሳሽ ደራሽ ሃገር አፍራሽ...





ደለል የሱዛ ሾባሽ
ከመረቦችህ ጋ ተዘረጋ.....
ከሰው መንደር ደርሰህ 'ር.ጋ።
ተጉዋዥ ነህ በጤፍ ጨረቃ...
የስደት ሰብአ ሰገል
ከርቤህ ነው የአፈር ደለል።
አ-ባይ አባይ...
አባይ-አ-ባይ....
አንተ ፈሳሽ ተንዶልዶዋይ
ያፈር ስንቅ አቀባይ
አንተ የግብጥ አድር ባይ
በቁምህ ራስህን ታይ...
በሰላሳ አመት በርሃ ...
አምሳያ ያገኘህ ውሃ።
ያም ሆኖ የኔ ጥያቄ ባጭሩ ይህን ይመስላል...
ይህንን በደል እያየ እንዴት ሃገሬው ዝም ይላል?
አፍንጫ ድፍን ሆነን ነው የተቸርነው ያንተን ከርፋት
ወይስ ክብር ሆኖን ነው ራስ መስበር አንገት መድፋት?....
ያም ሆኖ የኔ ጥያቄ....ይህንን ይመስላል ባጭሩ
ቴዎድሮስን መሆን እንጂ ጎንደሬነት መች ዳገተ
በላይን በፈጠር እንጂ ጎገሜነት መች አቃተ?
ብንብለጠለጥ በመንደር ሌላ ምጥ ሌላ ስቃይ ነው
ከሱ ሌላም አይፈጠር
ይልቀስ እንተባበር...አንድነታችን ይጠንክር
እሱ ነው ኢትዮጵያዊነት ያድዋ ድል ማግና ድር
እንተባበር ወንድ ይውጣ
አባይም ዞሮ ገነትን
ኤደን ኢትዮጵያን ያጠጣ።

## በቅሎ

በቅሎ...."አባትሽ ማነው"...ቢሉ'ዋት
"አያቴ ፈረስ ነው!" አለች...
ከ-አህያ መወለድ'ዋን
ልትክደው ቢያዳግታት
ልትዘነጋው ቢ'ያቅታት
ያቃታት ቢያቃትታት...
ለመናገር ቃል ያጠራት
ለአህያ ጭኑዋ'ን የሰጠች
ማህፀኑ'ዋን የተዶለች...
የፈረስ ልጅ አህ! ነች፡፡
እኛም እንደዚያች በቅሎ
ወንድነታችን ተሰልቦ
ግንዛቤያችን ጠቦ...
ባያታችን ከ-ረመሃይ....
ከቴዎድሮስ ወገን...ብንሆንም
ባባታችን ከነ መለስ
ካህያም ያህያ ልጆች..
ለባዕድ ጭን የከፈትን
ኢትዮጵያዊነት ያጠጠን
ፍርሃት ያቀነዘረን
ልብ አልባነት ያለዘበን
"ሉጢ" የምንትስ ልጆች
"ምንትስ ነን"፡፡





በሹካ መብላት ያስተማርን
የአውሮጳ' ስልጣኔ ታሪክ መስሎ የተሰማን
ባ'ህያ ጭን የሳትን
ጭንጋፍ የታሪክ ፍናፍንት
ድውይ የክብር ዳፍንት
ርካሽ ያን'ድንት ውግምት...
የማናውቀውን "እከሌ"
የተሸከምን እሽኮለሌ...
ከበቅሎም የበቅሎ ጠባይ
ፈረስ አይሉን
ካህያ ዋይ
አህያ አይሉን ፈረስ ጠባይ...
ከዚህም ከዚያም..."አዋይ አዋይ"
የሽርሙጥና "አወያይ"
የታሪክ... የዘር ደም ብካይ
ብካይ የጀርባ ተባይ
የተገዢነት ስር ንቃይ
የመፈራረስ ድንቅ ራዕይ...
ከበቅሎም የበቅሎ ጠባይ
ካ'ህያም ያህያ ከፋይ
የባርነት መዘከሪ'ያ
ፅኑ ጽልመት ጥርብ ድንጋይ...
"በቅሎ" በምድርሽ ላይ ጠባይ...
በቅሎ ጠባይ...፡፡
ሃፍረት የማናውቅ ጉደኞች
የጠገብን ለ'ሃብተኞች
የጭ'ለማ መንገደኞች...
የቅርስ የድርሳን ቀበኞች...
የ' ኢትዮጵያዊነት ደመኞች፡፡

ነቀርሳ በስንቱ ይወሳ
እንዲህ ታሪክ ተጨማልቆ
ብዕር እ'ናንተን ያንሳ?
አፎት ጫፎቱ ዶልዱሞ
መክተቢያው ቢሆን ቃሬዛ...
የሸተት የገለማ
ይህንን እየኖሩ ሬሳ
አረ!..ወደዚ'ያ።
በቀሎ ጠባይ
አህያ ውግ...
ያህያ ጥግ...ያ'ህያ ልክ...
ተንበርክከን ጭን የሰጠን
በዘር በጎሳ ንትርክ...
ፈረስን መሆን ያቃተን
አንሡን ወርደን መንደርተኞች
ካድዋም ያድዋ ልጆች
የሸሬ ልበ ጠባቦች
ያ'ዲግራት ሰፈርተኞች
የራማ 'ርጉም ስል ቅጥረኞች...
ካህያም ያህያ ለጆች....!!!
የወል' ቃይት ውልቅ ጥርቦች
ከጎንደርም...የ-ጎን-አደር- ልጆች
ግማሽ አማራ ትግሬዎች
ትግሬ ያ'ልሆንን አማሮች
ያጠበቡን ጥበበኞች....
ግማሽ ባሪያ
ግማሽ ንጉስ
ግማሽ ቅ'ማንት
ግማሽ ንጉስ....





ግማሽ መል -አክ ግማሽ እርኩስ።
ከጎጃምም...ጎጀን አሚዎች
በበላይ ስም ሃሜተኞች
የበቀል የቁርሾ ዘቦች።
ከሸዋም የሸዋ ሰዎች
የነገር ትንታግ እርኩሶች
የበላይነት እልቢሶች።
ከወሊጋም ወላ-አጋ-ዎች-
የምርጥ አሮሞነት መስፈሪያ
"የሚሽን" የቤት ስራዎች።
ከሱማሌም -ሱማ-አሌዎች-
የኡጋዴን ግንባርተኛ
የባርነት ነፃተኞች።
ከጉራጌም- የጎራ -አጌ-ዎች-
የማነንት ዘመናዊ
አጉራ ዘለል ሱልጡኖች
የካሊፍ ግማድ ሱልጣኖች
የትናንት ኢትዮጵያዊያኖች
የዛሬ የሰልጤ አረቦች።
ለአህያ ጭን የከፈትን
በ'አህያ የተዶልን
አህያ ያ'ህያ አጥንት
ጋማ የጋማ ልክፍት....
እርግጫ የ'ርግጫ ስርር
በቅሎ ነን የምብርክክ ቁጥር።
ታሪክ የሌለን ጀግናዎች
ነፃ ያልወጣን ነፀኞች
እርኩስ ያ'ርነት ኩስ
ዝገት ብል የታሪክ ብስብስ...

ያህያ ል የጋማ ውርስ
እምብርክክ ያህያ ውስብ
ማህን ማህፀነ ስልብ...
በቅሎ ጥርብ!
የልም ግት ነን አኬል ዳማ
የታርከ ጭን ባህያ ውግ
በኛ በሴሰኞቹ
በፍርሓት ሴተኞቹ የሚደማ።
እርኩስ ነን የትዝብት ውርስ
የባርነት ማሰሪያ አንቀፅ
የክህደት... የመሆን ግስ።
ከንቱ ነን ርካሽ ስጋ
የጠባነውን ጡት ነክሰን
አልፈን በጥርስ የምንወጋ።
ምንዱባን ነን ብሶተኛ
ለተንኮል የ'ማንተኛ....
ያህያ ልጅ ብሶተኛ
የማንነት ግዞተኛ።
ጋማ የጋማ ዘራፍ
አህያ ያ'ህያ ግርፍ
ብሶት ነን የተፈጥሮ ግፍ...
በቅሎ ነን ያህያ ቅንፍ።
ያህያ ልጅ የጋማ ውርስ
ዝገት ብል የታሪክ ብስብስ
እምብርክክ ያህያ ውስብ
መሃን መ'ኃጠነ ስልብ...
ከበቅሎም የበቅሎ ጠባይ
ካ'ህያም ያህያ ከፋይ
የባርነት መዘከሪያ





ፅኑ ጽልመት ጥርብ ድንጋይ
የነፃነት 'ርጉም ራዕይ...
የመታፈሪያችን ዕኩይ
የማፈሪያችን ተምሳሌት
በቅሎ ጠባይ
ታሪክስ በናንተ "ዋይ-ዋይ"
አዘመን ጉድፍ
'ርጉም ስራይ....
የምብርክክ ልጅ በቅሎ ጠባይ...
አይይይይይ!!!

## ሰዬመ እግዚአብሄር

የጥቁር አፈር ሠንበሌጥ
ሲመዘመዝ ሲወሰወስ
ይወለዳል ጌጥና ፈርጥ።
ጥቁር አፈር እርሱን ዘርታ
ዘር አድርታ...
ዘር አፍርታ........
የተዘራው ደሞ ደርቶ.....
ባረንጉዋዴው መቀነቱዋ
በለምለሙዋ ላይ አሽቶ.....
ዕውነትን ከሆዱዋ ሰፈር
ከሽንት ውኀዋ ተጋርቶ
አንድነቱዋን ከታሪኩዋ
ውበትዋን ከምነቱዋ ከቶ...
ነብሱን ለክብሩዋ እንደ' ሰለት
ጀርባውን ለሳት ሠንሰለት
ዕጅ ዕግሩን ደሞ ለብረት...
የዘመን ደዌ ሲያዝበት
ግንባሩን ላርማጮሆ ንዳድ...
ለመትማ የቀተር እሳት...
ስንቱ አለፈ....
ግን እያለፈ ግዘፈ.....
የትናንት የአበው ተስፋ
የግዜን ገደብ አለፈ....
ህያው...ይኸው...
በኔ በትናንቱ ሽል ነብስ ዘርቶ ተነደፈ......





የሰማዕታት ሕያው ድምፅ
ቃል ሆኖ በውስጤ ቢሰርፅ
ሚስጥረ ትግሉ በርትቶ
ህያውነቱ ጎልብቶ...
ጎልብቶ ቀልቤን ቢገዛው
ይሄ የህዝብ ተግል....
ይሄ የአበው የ'ደም ስር
ብዕሬን ስንኝ አዘራው።
አንጉዋዬ በትዝታ ምጥ...
በምናብ አለም ዝምታ
ፀጥ ባለ ተስፋ ሲናጥ
በማይታይ ትግል ሲዋጥ....
ምድሪቱ ወንድ ተነፍጋ...
አድባሩ ዘራፍን ሲያጥጥ....
ቀን ያሳሰበው ዐድር ባይ...
ሆዱ የሸጠው አታላይ
በርጬሜው ላይ ሲፈናጠጥ...
ያኔ ነው ባንተ ትዝታ....
ስንኜ ቃል የሚፈታ....።
ያኔ ነው የኔ ዝምታ
ጬኸት ሆኖ
ግጥም ሆኖ
ስንኝ ሆኖ የሚፈታ።
ሰውና ሰው
ያገሬ ሰው
አሙዋሙዋትህን ስሰማ
ሽል ሳለሁ ተንፈራገጥኩኝ
ነብስ አውቄ የልህ ምራቅ
የቁጭት ብሶቴን ዋጥኩኝ።

ሰውና ሰው ያገሬ ሰው
ኢትዮጵያዊነት አይደለም
በአጉል ተሰፋ መደንበር
ተገነጣጥሎ መያያዝ
ዕምነቱንም ማደናገር
ጥንትም ቢሆን የሳት ራት ያው የሳት ነች
ስሙዋም የሳት ነው ስትበር
ብሎ በሸንጎ መንገር
የብሶታቸው ባህል ነው
በንዲህ ያለው ጎቅ ማበር
ስዩመ እግዚአብሔር ለመሆን
ከዘመን ዘመን ለመኖር...
አይ ሀሊና ድንቅ ምናብ
ቀመናንም አለማፈር...።
ትናንት ከሆዱዋ ወጥቶ
ራሱዋ ላይ አመድ ማቡነን
መመፃደቅ መተናተን
እግር ተከተሎ መጥቶ
ጌታቸሁ ነኝ ስገዱልኝ
በልባችሁ መንበር ሹሙኝ
በምነታችሁ ላይ ሰይሙኝ
ሳትወለድ እደግ በሉኝ
እነ'ዕንትናም ዕዩኝ ዕዩኝ
ደሞ እኮ አድባራችሁ ነኝ
የናት ያባቴ ከራማ
በሕዝቦቼ ላይ የሾመኝ
ነግሶ ለመሆን ደጅ አስጠኝ.....
እኔስ እል ነበር የሸጠኝ
የራሴን ገፍቼ ከሰው...





የሰውን ሲያስቀላውጠኝ.....
እንዴት ዕላለሁ የሾመኝ
በዘረኝነት በሽታ...
ልቤን በንቀት ሲገልበኝ
የተገዢነት ልበና
እንደ ዡማ ፈረሰኛ
ወንበር ላይ ሲያገላብጠኝ....
መቀመጨያዬ ካናቴ....
ከማሰቢያዬ ሲበለጠኝ.....
እንዴት እላልሁ የሾመኝ....
እኔስ እል ነበር የሸጠኝ....
ብሎ በሸንጎ መንገር
የዲሞክራሲው ባህል ነው
በንዲህ ያለው ጎቅ ማበር...
ወደ ግዞት ለመወርወር.....
ስዩም እግዚአብሔር ለመሆን...
ከዘመን ዘመን ለመኖር....።
የውኃ ላይ ኩበት ቢያምፅ
ዕበት ሆኖ ትል ይወልዳል
የናንተን መብከት ለመግላፅ
በያመቱ በየካቲት
ትግራይ ከበሮ ይመታል...
ግማሽ ጎገሬው በችጋር
በምግብ ዕጦት ይሞታል....
ብሎ በሸንጎ መንገር
የብሶታቸው ባህል ነው
በንዲህ ያለው ኃቅ ማበር
ወደ ግዞት ለመወርወር
ስዩመ ዕግዚአብሔር ለመሆን

ከዘመን ዘመን ለመኖር...።
ለመግዛት ግዛት ለማስፋት
በዘር ጠርቶ
ከወርቅ መኃለቅ ወጥቶ
ምንድን ነው በድንበር መስፋት...
ህዝቡን ጠልቶ
ከመሬቱ ጋ!...መጋባት.....
መሬት መግፋት!
በስጋ ሳይዛመዱ
በኃሳብ ሳይላመዱ
ከልብ ሳይዋደዱ
ምንድን ነው ከንቱ መደንፋት
በሰው መሬት ከብት መንዳት
የማይገፋውን መግፋት
ሰው አጥር ላይ...
እግር ማንሳት....
ምንድን ነው ከንቱ መደንፋት
ወርቅ ከሆኑ ወርቅ ነው
የምን አፈርን ፍለጋ
መኖር ነው በወርቅ ሙዳይ
ባሸዋ በድንጋይ ዋጋ!
ለራያው ነው ለጎንደሬው
የሚጠፋው ያፈሩ መልከ
ላርማጮሆው ነው ለሳንጃው ሰው
ግር የሚለው የወርቅ እከክ....
ላፋሩ ነው ለኩናማው የሚጠፋው የከብቱ ልክ....
ካልሆነ እንጂ ገልምቶ ጥርኝ ነኝ ብሎ መታከክ...
ዝባድ ላይሆን የ "ወርቅ" እከክ
አንድነት ለጠኔ መውጫ...ለችጋር ማምለጫ ሲሰብክ





ሲመቸው ሙጨዩ ዘሪጋ...
የራማ የዛር አለንጋ....
ማጣፊያ ሲያጥረው ከንብልብል
አፋሽ ተንፋሽ ያባይ ደለል...
ጋብ ሲልለት ዝብጦ...
የተቀረው ጥቁር ወይጦ
ምንድን ነው እንዲህ መባዘን....
እሳት ሆኖ ወርቅ መምሰል?...
ወርቅ ከሆኑ ወርቅ ነው
ምንድን ነው እንደ ዕባብ መሳብ
ለወሰንና ለድንበር
ቁራጭ ማንነት መኀተት
የማይመስል ጎረግ መሳብ....።
ወርቅማ ጥንትም ወርቅ ነን
የነጠርን አሸንክታብ
የትንታግ መኃለቅ ትብታብ...
ገፍላ የገፍላ ድባብ...።
ወርቅ ከሆኑ ወርቅ ነው
ግማሽ መደብ ግማሽ ነሃስ...
ዕርጉም ተፈጥሮን ለማረስ
...በመሬቱም ላይ ለማረስ።
ብሎ ብሸንጎ መንገር
የዲሞክራሲው ባህል ነው
በንዲ ያለው ኃቅ ማበር
ወደ ግዞት ለመወርወር
ስዩመ ዕግዚአብሔር ለመሆን
ከዘመን ዘመን ለመኖር
የሚውተረተር ጅራሬ...
ብሶት ያጸናው ጎፈሬ...

ብሶት ያጎለመሰው...
ሃያ አመት ሆድ እንደባሰው
አንድ ቀን ሳይኖር እንደሰው...
አንድ ቀን ሳይባል መሪ
ሃያ አመት ቁስሉን ሲያወራ...
ይህ የ-እነጎ አባወራ....
የንጥቂያ የግፊያ አውራ...
ኢትዮጵያ ያንቺ መከራ....

*(መታሰቢያነቱ ስለ ኢትዮጵያ አምብኝ ብለው ለሞቱ አሁን በእሰር ላይ ላሉት እኩያን ላልሆኑት ኢትዮጵያዊያኖች)*





## ምን ትል ነበር

በቅሎውን እየገረፈ
ቅኔውን እየዘረፈ
ልጁ ድክ ድክ ሲል ከሁዋላው....
ይታየኛል...አባወራው፡፡
ጥላ ፈልጎ ሲቀመጥ....
ለመሬቱ ሞፈር ሲቆርጥ....
ይታየኛል....
የበተነው ሰብል ሲሆን
የጨበጠው ጥሩ ፍሬ....
የዘራው ለዘር ሲበቃ....
ሲ'ያበራይ...ዞሮ ሲወቃ.....
ይታየኛል...
ማልዶ ማህሌት ሲቆም
ጾመ ህዋሪያን ሲጾም
ዘንግ ሲወረውር ሲጸነጽል...ጸና
ድጉዋ ጾመ ድጉዋ-ሲቀኝ በበገና፡፡
ይታየኛል ዛሬም የደረበው ካባ
አውዱ ላይ መቅረዙን ለኩሶ ሲገባ....፡፡
የትከሻው ሞገስ....የፊቱ ብርሃን
የቀሚሱ ሽታ....የውበቱ ጸዳል....
ይታየኛል ዛሬም....
እጁን ሲያሳልመኝ....
እግሩ ላይ ቁጭ አርጎ ፊደል ሲያስተምረኝ....
ሃገርህን ውደድ....እባትህን አክብር....

በባልጀራህ ላይ...ክፍ እንዳትውል....
እያለ-ሲሰብከኝ...
ይታየኛል ዛሬም...
መሰንቆ ሲመታ....ክራር ሲከረከር
በ-በገና እንደበት አምላኩን ሲያከብር.....
ይታየኛል ዛሬም
እስመ ለእመ ርጎብነ
ወጸማእነ ወአረቅነ
ን-መንና ለስጋነ ከመ-ትድሃነ ንፍስ-ነ
ቃልህ በውስጤ ገነነ
ትዝ አለኝ....ትንሳኤ ግእዝ...
ሃጣዓን ...በቃሉ ሲወገዝ
ፊደል ከገመደበት ...ከሳት ሰንሰለት ትናጋው....
ማልዶ አሃዱ ስላለ....ሰይጣን ጽናቱን ሲዋጋው.....
ቁዋንቁዋው ሳይደበልቅ....እንደባቢሎን ሳይናድ.....
ከነበረበት ፈቅ ሳይል....የጀልባው መናጥ ሳይንዳው....
ነነዌን ከጥፋት ሲያድን...
ቀይ-ባህር ከጠላቶቹ...ከግብጽ እናት ላይ ሲከደን
ከምነቱ ጋ ኖሮ ሲሞት....
ያስተማረኝ ትልቅ እውነት...
ፍንትው ብሎ ቢታየኝ...
ዛሬም ካህኔ ትዝ አለኝ።
ዛሬም ካህኔ ትዝ አለኝ
ጽላቱ ክብር ተነፍጎ
ቅርሱ መዛግበት ድርሳኑ....ትውፊቱ ሁሉ ተሰርቆ
እትብቱን የቀበረበት
ደሙን የገበረበት
ዕልፍ አዕላፍ ህዝብ ያለፈበት
ያ የዘመን ትለቅ እውነት....





ያ-የዘመን አብይ እምነት
ጣይ እጣ ሲጣጣልበት
ፊደል የፈደፈድኩበት
ቅኔን የተቀኘሁበት
ፍቅር የተጠመኩበት
እኔን ሁኜ የኖርኩበት
ያ የዘመን ትልቅ እውነት
ፊደል በስንጥብ ቁልቁል እያበከርኩኝ ስገፋ
አንገቴን ከጽላቱ ፊት...ለ'ክብር በፍቅር ስደፋ
ፊደል ማለት በል ስትለኝ
ስከተልህ ስትመራኝ
ፊደል ማለት...
አንተ ከኪዳነ ወልድ
እኔ ደሞ ካንተ ጥበብ ካንተ ቅኔ ስር ስወለድ
ፊደል ማለት በል ስትልኝ
ፊደል ማለት ብዬ ስልህ
"አምሳያ ወይም ምልክት
የቃል መልክ የቃል መስታወት
ከፍሬ ምናጦስ ወዲ' አበገደ የነበረውን
ሀ-ለ-ሐ-መ ብለውን
ከላይ እስከታች ያፋለሱት
ተርታውን ያወሳከቡት
ጽር-እውያንና ቅብጣውያን
የግእዝ ፊደል በአሃዝ...
እናዳይቆጠር ፊር እንዳይዝ
አሃዱ ከሌቱ ብለው
የአልፋ ቤት ጋማነቱን
ከሰባ በቀር ሰርዘው
ደሞ-ሮ-ሚከሮን ብለውን...."

እንዲህ እያልክ ስትነግረኝ
አንተ ሞተህ ስታኖረኝ
"የቃል ህብር የቃል እውነት"
"የቃል ግብር የቃል እምነት"
ሲወሰውስ ያ ሰዋሰው
ብራናው እንከዋ በቅኔህ ደረቅ አንዠቱን ሲያርሰው
ከሰውም ሰው ያገሬ ሰው
የኔ ካህን የኔ አንድ ሰው
ዛሬ በህይወት ብትኖር
ምን-ትል ነበር ትለን ነበር
እንደምን ያለ ብሽታ
ቤተስኪያኑም ተቆራርሶ
በአህዛብ ሴራ ሲመታ
ምን ትል-ነበር ትለን ነበር።

*(ለአለቃ ዘነበ የአበገደ አባቴ)*





## እንገቱ ተጣሞ ቁምጣ ተሸከሞ

የወገቡን ክፈፍ ከሲጋው ለጥፎ
ቁምጣውን  ከቆዳው ዘምዝሞና ጥፎ
በላሌውን ይዞ....ለዘመን የኖረ.....
ሃርነት የሚባል... አንድ ተባይ ነበር።
እናም ይሄ ተባይ..
በቀን ከሚሰጠው....ጥቂት የደም ድርቆሽ
እየመጠመጠ የብሶቱን ጥሎሽ
ተራራ እየወጣ....ጫካ እየወረደ.....
አንዳንዴም በሞርታር አብሮ እየነደደ.....
አስራ ሰባት አመት...ቁምጣ ተሸከሞ
ከተማ ደረሰ...አንገቱ ተጣሞ።
የከተማ ኑሮ...ጠማማ አንገቱን
የጠማውን ውሃ የጫካ ብሶቱን
እልሁን መግለጫ ገና እንደደረሰ
ድመት ቢመነኩስ አመሉን ላይረሳ
ተባይም ከላቡ...ኩ-ድፉ ላይነሳ
የለመደበትን የተባይነቱን...
ያራግፍ ጀመረ እከካም ህይወቱን።
እና ይሄ ተባይ.....
ሲኖር ሲኖር ሲኖር
መመጠን ተስኖትን ሲነክስ ሲቀዳ
የጠጣው ደም ነፍቶት አብጦ ሲፈናዳ
ጠማማ አንገቱ ይ-ቃና ይመስል
ብጫቂ ብሶቱን ትግል ብሎ ሲስል
ድንጋይ ስር ተረግዞ...ቁምጣ ላይ ተወልዶ

የዘመን ብሶቱን...ኩ-ላብ ስር መንቃቱን
ትንፋግ መጠመቁን....በመዳፍ መፋቁን
ሲፎደር ሲጨመቅ....ሲዳመጥ በጥፍር
አብጦ ሲያንቦጉብ ገላ ላይ ሲቁዋጠር...
መሆኑን ዘንግቶት
በደም የታጠበ ያ-ህያ ውሃ ጠጪ
ቁምጣ የለበሰ የተባይ ነጻ አውጪ
በማያቁት ሃገር ሲጠይቅ ቁርበቱን
ወርቅ ነኝ ጨርቅ ነህ ሲልህ ባንደበቱ
ነግሶ እንኩዋን ተባይ ነው አናት ላይ የወጣ
በደም የታጠበ ደም ገፍቶ የመጣ።
አስራ ሰባት አመት...ቁምጣ ተሸክሞ
ከተማ የደረሰው...አንገቱ ተጣሞ።
የነጻነት ፊሊት አመጽ አስኪነፋ
በሰው ደም ንከሻ አብጦ እንደተነፋ
ብሶቱ ገድል ሆኖት ሁሌ እንደደነፋ
ይኸው ዛሬም አለ ቀብሮ ያ'ገር ተስፋ።





## እሱን ስመለከት ግጥሜ ተቋረጠ

እንግዲህ ግማሽ ቦጠሊከኛ ነው
ትንሽ ትንሽ የሚነደው ትንሽ ትንሽ የሚይስፈራው
ደሞ ልጆች ወልዶዋል
ባህር ማዶም ሲኖር ሃገሩ ላይ ትንሽ መሬት ነገር
ገዝተዋል።
ታዲያ ይሄ ሃብቱ...እሺ ጌቶች ብሎ ያፈራው ንብረቱ
ከጥያቄው ጋራ እየተጋጨበት
ከስሜቱ ጋራ እየተምታታበት
ሰልፍ እንኩዋ ሲሰለፍ ፊት ለፊት አይቆምም
ገፁን ሁኔታውን መልኩን አያሳይም።
ብቻ ሲመሽለት መለኪያ ሲያነሳ
ያሃገሩ ነገር ካንደኛው ማዕዘን እንዲሁ ሲነሳ
ጠረጴዛ ይመታል
ብሶቱን ለመግለጽ ምራቁን ይውጣል
መለኪያ ይጨብጣል
አልኮል ይጨልጣል።
ግማሽ ነው አካሉ
ሃገሩን አይጠላም ለመውደድ አይደፍርም
ግን እኮ ሲነደው ሰንደቁን ይለብሳል
ትንሽ ይቆይና ንብረቱን ያስባል
እዛው በተቃርኖ በግጭት ይላሳል
አዝማሪው ሲገጥም አይኑ እንባን ያቀዛል
ፍቅሩን ለማሳየት ከዝማሪው አንገት ስር

ብሩን ይሸጉጣል
ትንሽ ይቆይና....ከፍርሃት አለም
ከማያውቀው ቅዠት ገብቶ ይሸነጣል።
ግን እኮ ፈሪ ነው
ኸ-ጠላቶቹ ጋ ቀጭ ብሎ ይጠጣል
ይሄ ቢሆን ይሄ....ይዋያል ስ'ላገር
ከቀባሪዎቹ በቁም ከገነዙት
አጥንቱን መንዝረው በጎጥ ከሚያምሱት
ከነዚያ ጉዶች ጋ ጠበል ይጠራራል።
በደሉን ረስቶ ወይ በደሉን ፈርቶ
ከበሮ ሲመታ
እንክሽ እነካ ያስነካል እስክስታ።
እሱን ስመለከት ግጥሜ ተቋረጠ
ስሜቴ ቀጣዩን አንጉዋዎች አማጠ።
ጅራፍ ነው ስሜቱ
እንባ ነው ጉልበቱ።
የፍትህ ተጨቁዋኝ የነጻነት መናኝ
የራሱ እስረኛ አልቃሽና ዘፋኝ
ትናንትና በጋኝ አክንባሎ ገፊ
ምጣድሽም ዜር እንትንሽም ዜሮ የዜሮ ዘራፊ
ዛሬ የቅንድብ አሽከር ቅማል አሳላፊ
ሽፋሽፍት አሞጋሺ...የዘሮ መከደኛ ባዶ ወስከንባ ሰፊ....
በዜሮ ወንፊት ላይ ዜሮ እንክርዳድ አንፋሽ
ዜሮ ታሪክ ነፊ ዜሮ ታሪክ ገፊ።
ማነህ
አንተ ያይን ጭራ ኩል
ሶሎግ ሰባራ ስንኩል
የፅናት የጀርባ ቅማል
ስጋ ቁልል



ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም

ስጋት ድልል
የሕውሃት የድልህ ድልል
ሽቃጭ ያፍ ቅምጥል
እራፊ ያቋም ብጥል...
ማነህ?
ሆንህ ከረምክ አሉ ትልቅ ባለቅኔ
ለዚያ ለዘመዴ ለዚያ ለወገኔ
ቁርበት ላይ ለተኛው
ድብዳብ ለለበሰው
ብራና ለፋቀው ፊደል ላረቀቀው።
ግጥሙ ተቋረጠ
ስሜቴ ቀጣዩን አንጉዋቆች አማጠ....
ሲመሽ አስረስ ምቺው
አሼሼ እስክስታ
ሲነጋ በንዴት
ግድግዳ በቡጢ
ግድግዳ በርግጫ
ግድግዳ በቴስታ።
ሲመሽ ተፋፍቶ ተጠራርቶ አምባ
ተጠራርጎ አምባ
ሃገር በመለኪያ ተንቆርቁሮ ካንገት ከሆድ እንዲገባ።
አጋፋሪው ዘራፍ
ተጋባዡ ጎራው...ብቅል ሆዱን ሲያ'ባው
ስንቱ ተቆርቋዋሪ የመሸታ ታጋይ መጠጡን አነባው?
ታሪክሽንማ አንገበር ማፍረሻ
የስጥ ሸሮ ፍትፍት ልሳን ማላወሻ
ካረጉት ቆይቷል
ለሰሚ የሚገርመው ለተመለከተው
መለኪያ ጨብጦ ጅግናም ሆኖ አንዱ ሰው።

እንግዲህ ሃገሬ በይ እርምሽን አውጪ
ምንገድሽ ተይዞዋል
ግማሽ ልቡ እስከስታ
እኩሌታው ጫካ
በሆነ ነጻ አውጪ።
ነጻማ ነጻ ነሽ
ብዕልፍ መስዕዋት የተከበርሽ እናት
ያ'በው ያጽም ውርስ
ማህተብ የሆነሽ የነጻነት ክትብት
ነጻማ ነጻ ነሽ።
ስምሽ ጎደፈ እንጂ ክብርሽ ክብርን አጣ
መለኪያ እያጋጨ ሱረት እየጠጣ
የተነሳ ጊዜ ነጣ አንቺን ሊያወጣ
ክብርሽ ክብርን አጣ።
የዘንድሮሽ ታጋይ
የዘንድሮማ ወንድ
ፋኖው የጭን ገረድ
ትክሻ መንቀል ነው
በርሃው ዳንኪራ ባቲ እክስታን መውረድ።
አንቺማ ነጻ ነሽ
ከሼባ እስከ-ቃዴስ
ከሱዝ እስከ-አርጤሚስ
አቭድና ሆመር
መጽሀፈ ሄኖክ መጽሀፈ አስቴር
ህዝቅኤል በራዕይ
ዳዊት በውዳሴው በመዝሙር ምስጋናው
ሙሴ በኤርትራ በኮሬብ ምድርም ላይ
የመሰከሩልሽ ሃገሬማ ሀገር ነሽ።
ሀገሬማ ሃገር ነሽ





በምሰለ ማክዳ ለንጉስ ሰሎሞን ጥፍጥፍ ወርቅ ያቀረብሽ
አፈሬማ አፈር ነሽ።
ስምሽ ጎድፈ እንጂ ገጥታሽ ወየበ
በችግር በራ'ቡ የመልከሽ መስፈሪያው አርብሽ ተመጠነ
ባውሮጳና ኤሽያ ሽግርሽ ሲበተን
እውነትሽን ሲያውቁ
ታሪክሽን ሲያውቁ
ትናንትሽን ሲያውቁ
በዛሬሽ ያሙሽን
ቤትሽ ቁጭ ብለው
ታፈርሽ ላይ በቅለው
ሊሰሩብሽ ኖረው
ቀልብሰው ዝናሽን
ሽጠው ታሪክሽን
አቃጥለው ቅርስሽን
እንደ ሰደድ እሳት በሚበላ ትንታግ እየተራቀቁ
ፅንፉ እንደገባቸው ጽንፉን እንዳወቁ
እነሱን አስቤ
ታሪክሽን አስቤ
ዛሬሽን አስቤ
ደሞ ይሄ ወንደሜ ያንን ክብርሽን አንቺን ያላወቀ
ጀግና ነኝ የሚለኝ የብርሌ አንገት ጠርሙስ እያነቀ።
ይህንን አስቤ
ደሞ ያንን አስቤ
የጥንት የጠዋቱን
"ማርያምን ላልምርህ" በማሪያም ተምሎ
ስንቅ በስልቻ ስንቅ በቀልቀሎ
ነጋሪት ሲጎሰም
ከበሮ ሲመታ

ባጥንቴ ተዋርሶኝ ዛሬም ይታየኛል የፈረሱ ኢስክስታ።
እንግዲህ ሃገሬ በይ እርምሽን አውጪ
ሰንደቅሽ ተይዞዋል ግማሽ ልቡ እስክስታ እኩሌታው
ጫካ በሆነ ነጻ አውጪ።
ግጥሙ ተቋዋረጠ
ስሜቴ ቀጣዩን አንጉዋዎች አጠጠ።





## ንገረኝ እንግዲህ

ንገረኝ ኢንግዲህ ወገብህን ታጠቅ-አንተም ተናገርኝ
ሰገሌ ላይ ስሞት
ጉንደታ ላይ ስሞት
መቅደላ ላይ ስሞት
አድዋ ላይ ስሞት....
ነበርክ መሰለኝ...?
ንገረንኝ ኢንግዲህ...
የድርቡሽ ወጥቶ አደር
የግራኝ ወጥቶ አደር
የጥልያን ወጥቶ አደር...
ልቡ እንደሰም ቀልጦ ጉልበቱ ሲራገብ
ቆጥረከዋልና የደሙን ነጠብጣብ...
እኔም ልጠይቅህ ወገብህን ታጠቅ....
አንተም ተናገረኝ...።
ንገረኝ ኢንግዲህ....
አንተ ነበርክና...
ሬሳው በሳንሳ.
..በሽክም ሲነሳ....
ስይፌ ተሰገባው...ተመዞ ተጎድኑ...
ተሰርጡ ሲገባ።
አንተ ነበርከና
ነብሱ ስለቴ ላይ ተንሸራቶ ሲፈስ
ህልሙና ሽንፈቱ ሞትን ሲተነፍስ....
አንተ ነበርከ አሉ
በድኑ እንደሽት...ከመሬአት ሲታፈስ...

አንተ ነበርክ አሉ
እንደጠፍ ዘመመን የወደቀ አካሉ ሌላ አካሉን ሲልስ።
ሎሚው ተንቀጥቅጦ
ግልበቱ ተሙዋጦ
ሃይሉ ተፍረከርኮ ጅማቱ ሲጋይብ
ገላገልከው እንጴ ያ ቆዳው ሲወይብ?
ንገረኝ እንግዲህ...
ምህረት ተነፍጎ ብርክ የያዘው ለታ....
የኔን ኢጅ ቀምሶ ዝናሩ ሲፈታ...
አንተ ነበርክ አሉ....መንገድ ያሳየኸው...
ባበሻ..እምቢታ....እሳት ያስበላኸው....።
በላ ንገረኛ....
ምን እንደሚመስል....
ሰው ሃገሩን ሲክድ....ሰው ሃገሩን ሲጥል....
እባክህ ንገረኝ....እንግሊዝን መርቶ....ከመቅደላ መድረስ....
ለጥልያን ሰግዶ....ጥሬ እንቁላል መጉረስ....
ያዲያቆነ ሰይጣን አይለቅም ሳያቀስ....
የባብ ልጅ እባብ ነው....ከጉልበትህ የወጣው....እሱም ቀን
ጥሎለት የኔን ሃገር ያፍርስ?....
ንገረኝ እንግዲህ....
ማነህ ቢሉህ ምን ነኝ ብለህ ታወራለህ....
የከበሮ ህይወት ከበሮ ማንነት....
መጥፊ እየሙቱ የሚዘምሩበት.....
የራስክ ድምጽ የለክ
የጠፍጣፊክ ልሳን....የጠፍጣፊክ ግብር
አውሮጳ ተቀኝተህ....አዲስ ላይ እጅ አዙር።
ፊት አዙር ከበሮ....ፊት መልስ ለጥፊ....
እንቁላል ነው ግብርህ ላንተ አይነት ቀጣፊ።
ፊት መልስ ከብሮ.....





ትናንትና...እባብ የጫካ ቀበሮ....
ዛሬ....እንቁላል ልሶ....ህዝቦቹ ላይ ሰክሮ.....
ነገ ሲወረወር....ደሞ እንገቱን ሰብሮ.....
ፊት መልስ ለጥፊ ተጠፍጠፍ ቀበሮ።
እና ልጠይቅህ ወገብክን ታጠቅ አንተም ተናገርኝ.....
አትቀርምና አመጣጤን ሳታውቅ
በላ ልጠይቅህ ወገብክን ታጠቅ...።
ንገርኝ እንግዲህ
የነማን ፍላጻ...እነማን ልብ ውስጥ ተሰንቅሮ ቀረ....
የማንስ ጀግንነት የጥቁር ፈርጥ ሆኖ ዝንተ አለም ከበረ።
ንገረኝ ኢንግዲህ
የሰቀሰቅሁትን
የጠቀጠቅሁትን
የሸቀሸቅኩትን
በርምጃዬ ጭነት....
በዱካዬ ክብደት ያስከነዳሁትን...
ያንቀጠቀጥኩትን...
ንገረኝ ብያለሁ....
ሽምጥ ስጋልብ
ስምጥ ሰወጋ
ስሸልል ሳቅራራ...
እግሩን ስቀነጥስ
ቁዋንቁዋውን ስበጥስ
የጋማ ጠጉሬን አናተእ ላይ ስለብስ
አቡዋራው ሲነሳ
ክንዴንም ሳነሳ
ጋሻዬን ስሞግት
ልጉዋሜንም ሳብት
ጦሬን ስነቀንቅ

## ግን ለምን ነው የምወድሽ

ነጋ መሽ የማስብሽ
የምራብሽ የማነባሽ
ምን ተውሎልኝ ነው እኔ
ዛሬም የምለው ሃገሬ
ለምንድን ነው የምወድሽ
በብር ማንኪያሽ ተኝቼ...ቂቤ ባፍንጫዬ አልጠጣሁ
ኩራዝ አ'ስይዤ አልበላሁ
ጉልት ርስቴን አልተቀማሁ
እንዳ'ንድ ሰው ምን አገኘሁ
እንዳ'ንድ ሰውስ ምን አጣሁ?
የታሪክሽ ክብር እንጂ...ያንቺነትሽ ፍፁም እውነት
በትናንት ያ'በው መሰዋት የዛሬ የኔ አንገት መቅናት
እሱን ብዬ እንጂ ኢትዮጵያ...የኔ ባንቺ ክብር መኩራት
ያንቺ በኔ ትግል መፅናት
እንዲቀጥል ፈልኩ እንጂ....
አጅሬ በጦር ሲያቅተው ሰው በፈጠረው ቸነፈር
አልደፋም እምቢኝ ባልኩዋቸው....በራብሽ እኔ እንድሰበር
እኩይ አላማው ቢገባኝ....እምቢኝ አልኩ እንጂ ሃገሬን
አፈርሽ ፍቆኝ ነው ያደኩ 'ጣይ እየመታው ነውሬን።
ሺ-ጠመንጃ ያዥ ቆሞልኝ...
አሽከር ገረዱ ሰግዶልኝ
እንዲያ አይደለም ያደኩት





እንዲያም አይደለም የኖርኩት
ይናገር ለምለም አውድማሽ መዳፌን ልጩ ያ'ረሰኩት
ይናገር ሰንጋው በሻኛው ላብና አሞሌ ያላሰኩት
ይናገር ሰጋር በቅሎዬ...እልህና 'ህል የጫንኩት።
እንጂስ...ምን ቀርቶኝ ምንስ አግኝቼ እኔ
ትናንት ተይዤ በጠኔ
ከለምለም መስክሽ እሸቱን የሸመጠጠው እንቶኔ
መሬትሽ የሚታረሰው
አዝመራሽ የሚታፈሰው
መቼ በኔ ሆነና...
እኔማ የህልውናሽ የመፅናትሽ የስቃይ ድምጽ
ወርቅሽ በባዕድ ሲጠል እምቢኝ ብዬ የማምጽ
አንድ ምስኪን ከልጆችሽ አንዱ የሆንኩኝ
እንጂ መች ከበረከትሽ ከናትነትሽ ጠባሁኝ?...
መቼ ባንቺ ብረት አኔጥኩ.....መቼስ አንቺን እኔ አስኔጥኩ
መቼስ ሰላንቺ እንደልቤ የፍቅሬን ያህል ተናገርኩ....
እኔ እኮ አንድ ምስኪን ነኝ
ሰንደ'ቅሽን እንኩዋ እን'ዳለብስ ማእቀብ የተጣለብኝ
ሃገሬ ብዬ እንዳልጠራሽ ወንድሜ የደገነብኝ
እኔ እኮ አንድ ምስኪን ነኝ
ያርገኝ አልኩኝ እንጂ ለወጋግራ ለድግርና ለሞፈር
ለትንሳኤሽ የምሰዋ ለታሪክሽ የምገበር
በቁሜ በንቺ ድህነት ይህንን አንገቴን ከምቀብር
ለትንሳኤሽ ልሙትና ካፈርሽ ስር ልቀበር
አልኩ እንጂ.....እኔማ እማማ
እንዲሁ ዝም ብዬ የምወድሽ
እንዲሁ ዝም ብዬ የማስብሽ
ካድማስ ማዶ የማነባሽ
የምትርቢኝ የምርብሽ
አንድ ምስኪን ወንድ ልጅሽ

ግን ለምን ነው የምወድሽ?
...እኔማ
የትግልሽ ብርሃን ይመስክር
በእሳት ናዳ ከሰማይ...
ያ'ድዋ ቀዬ ሲጋይ
ራስ እምሩ ነብሱን
ራስ መንገሻ ክብሩን
ራስ ሙሉጌታ ደሙን
ያኔ በማይጨው ሰሞን
የተንቤብ ህዝብ በመርዝ ጭስ
በሰማይ ናዳ ሲታፈስ
እምቢኝ ሃገሬን እንዳለ...ከጥይት ጋ ሲጠራመስ
ታሪክ ጽናትሽ ተሰምቶኝ
ያሉላ ደም እኔን ሸቶኝ
የክብሬ መለኪያ ሆነሽ...ላንቺ ስሞት የምትኖሪ
ስትኖሪ የምቃና...እንደ አንድ ሰው ታሪክ ሰሪ
የሞሆን ጭንቀት ያስጮኸኝ
የፍቅርሽ ብሶት ያስነባኝ
ካድማስ ማዶ የማስብሽ
የምራብሽ
የማነባሽ
የምትርቢኝ የምርብሽ
አንድ ምስኪን ወንድ ልጅሽ
ግን ለምን ነው የምወድሽ?



ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም

## ወገቧን ያማታል

አምጣለች ጭንቀት ኖራለች መከራ
እጣዋ ሆነና ጭንቀቷ አያባራ
እምባዋ አያባራ።
ታለቅሳለች ዛሬም
ልጆቹን እያለች
አቡዬ እያሉ
መጥምቁ እያለ
ልጄ ምንም አትሆን
እንቅፋት አይመታህ
እሾህም አይወጋህ
ትምልልኛለች
የሃዘኗ ምክንያት
የደስታዋ እንቅፋት
እኔ ልጇ እንደ-ሆንኩ
ምን ያህል ታውቃለች?
እያልኩኝ ከራሴው
እነጋገራልሁ
"አልቅሼ ነግሬው ያንተንማ ነገር"
ታባብለኛለች
መሃል ላይ ሲቃዋ እምባ ሆኖ ይፈታል
ፍቅርና ብሶት ትዝታና ንፍቆት
ሳግንና ሲቃን ቀላቅሎ ይናጣል
ሲቃዋን ስታምቅ...የወገቧ ህመም አቃስቶ ይወጣል
እሱን ስትደብቅ ለቅሶዋ ያመልጣል
ምነው ድምጥሽ ብላት
የዘመኑ ጉንፋን

መስመሩ ይሆናል እንደገና ደውል
እንዲህ ትለኛለች።
ምን መስመር አለና የዘመኑ መስመር
በድርብ ፈታዮች የተፈተል ክር
ሲከር ሲተረተር
ትርትሩ ሲቋጠር
ቋጠሮው ሲጠለፍ
ጥልፍልፉ ሲዘንፍ
ወርቀ-ዘቦው ሲረግፍ
ታቋዋርጠኛለች...
ተወኝ ነገርህን ወዲያ ብዬሃለሁ
ይህንን ሃሳብህን ወይ ቁሜ ባላየሁ
ምን መስመር አለና ትንሽ ትስማማለች።
ልክ እንደ መስመሩ
እኔን አንድ ልጇን
ጠልፈው እንዳይወስዱኝ በውስጧዋ እየሰጋች።
እርቄ ባላያት
ዘመናት ቢቆጠር
በመቀራረቢያው ባየሩ ሰንሰለት
እንደምን ነሽ ብላት
ቆይቼም ብደውል
ሰንብጬ ከርሜ
ያወጋችኝ ነገር አየሩና ብርዱ
ብርዱና ሞገዱ
ከፍቅሯ አንሶባት
ልክ እንደ-ትናንቱ
ትንፋሼን ስትሰማ እንባዋ ቀደማት።
ያኔ እንከዋ በቀደም
ጡቷን ስመጠምጥ





እፎይ ማለት ቢያምራት
ግራዋ ቀብታ ጡቷን ብታጎርሰኝ
"ቱ" ብዬ ብተፋው
"እኔን ልጄን እኔን"
ጠላትህን ይክፋው
ብላ ከመቅጽበት
የቀባችውን ጡት የራሱዋኑ ገላ እየተራገመች
አጥባ አጎረሰችኝ ወገቤን እያለች።
"የኔ አለም ባሪያዬ"
ጥፍጥፌ እከሊሌ
ጡት መጥቢያ መዝሙሬ
ጠሩኑዋ ነበረ መልኩዋን መለያዬ።
ዛሬ ከሩቅ መንደር
አብሮነት ከራቀው
እኔ ትብስ አንተን ፍጹም ከማያውቀው
አፈር ከሌለበት አለት እየጫርኩኝ
ፍቅርና ብሶት ከጠጣሁት ጡቷ
ከነብሱዋ ተጣብቶኝ
ምን ነው ድምጽህ ልጄ ምነው ተቀየረ ብላ ብትጠይቀኝ
በናኙ ተናኙ የስደት በረዶ አየሩ ነው አልኩኝ።
ደግሜ ብደውል ዛሬም ታለቅሳለች
ምነው ድምጥሽ ብላት
"የኔ አለም ሳልነግርህ"
አንተሀ ከሄድክ ወዲህ አየር ተለውጦ
አልሰማህም እንዴ ከባቢው ተሟጦ
ወበቅና ሙቀት ቀዬህን አራቁቶት
ያ! ያደግህበትን መንደርህን ንጦት
መንደርህን ልጦት
“ምን መንደር አለና ምን አየር አለና....”

ትብከነከናለች
አንዳንዴ እኔን ነች
ተወው ይቅር ልጄ
እንደምን ነህ አንተ
"ሰኞ ለማክሰኞ በህልሜ አይቼህ
አውላላ ሜዳ ላይ ብቻህን ቆመሓል
አንድ ቀይ ረጅም...እሱ ሚካኤል ነው እጁን ጭኖብሓል"
አቁዋርጣታለሁ...
አይ እማሚ እናቴ
እንደኔ እንደ-ልጅሽ
መንገድ ለዞረበት ኑሮ ለዳገተው
ሃገር ለናፈቀው ፍቅርሽ ላጨመተው
ቁሞ እየሄደ በውስጡ ለሞተው
ህልምሽ ላሜ በራን ስንዝሮን ተረት ነው።
በህልምሽ እዛው ነኝ መቼ ተሳፈርኩኝ
መቼ ተለየሁሽ አውላላ ሜዳ ላይ ቁሜ ከታየሁሽ?
አሁን ያለሁበት መቼ አውላላ አለ
የተሰመረ ነው የተገጠገጠ
ፍቅርና ተፈጥሮን ሰልጥኖ ያጠጠ።
ቀይና ረጂም ሃገሩን ሙሉ ነው
እንዳንቺ ከሆነ እንደ-ህልም ፍቺሽ
ሁሉም ሺ-በከንቱን ሁሉም ሚካኤል ነው።
ትንሽ ትስቅና ማለቀስ ስትፈልግ
በሃምሌ አሳባ
በጥቅምት አሳባ
ወገቤን ትላልች ደሞ ልታነባ

$9.99
ISBN 978-0-615-65437-9
50999>
9 780615 654379


ሄኖክ የሺጥላ

የሄኖክ የሺጥላ "ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም" የሚለው መጽሐፍ የቃላት ውብት፤ የምት ዜማና የጥራት ጥንቃቄን የተሞላ ሲሆን፤ የድምፅ የለሹን ጩኸት የሚያስተጋባ ቁም ነገር በጉያው የቋጠረ፣ የትውልድ ተጠያቂነት ያሰጋው የግጥም ስብስብ ነው።
ገና መቅድሙን ሳነበው "እንኩዋንም ሳይፅፍ መኖር አልቻለ፣ እሰይ! ለኛም ማር አዘነበልን አልኩ"። አለበለዚያማ
"ከኢትዮጵያዊነት በታች መጥበብ አይችልም ስሜቴ
አርበ-ሰፊ ነው ቆዳዬ ማደሪያ የሆነው ለትብቴ...
ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም
በሞትሽ ላይ እኔ አልሽሽም"...አባባልን የት እናገኘው ነበር? የገበሬ ልጅነትን፣ የማንነት መሰረታችንን ሲያስታውሰን ደግሞ...
"የኔ አባት ገበሬው ሞትን የደፈረ...
ኖሮ የተማረ
እንቢኝ ዝባዝንኬ
ላገሬ ነፃነት አባቴ ነው ልኬ
አባቴ ነው መልኬ"ይለናል።
በነጋ በጠባ ቁጥር የውድ ሃገሩን ስሙዋን እየጠራ "አቤቱ" እያለ ታላቁን አምላክ በጥያቄ ሲማጸን ታገኙታላችሁ። በበቂ ሁኔታ ያልተከፋውን አለም ይጠይቃል...
"ንዴትን ያመን ከሆነም ንገሩኝ ምንም አይደለም..." ድንቅ ነው። ሔኖክን በዚህ እድሜው ያስቆጣው መራር እውነት አለ።
"እየጠፉ አለሁ ማለት
እየጠፉ ያልፋል ማለት
ተረት ትረት..."
እየጠፉ ከመፎከርና አለሁ ከማለት ያውጣን። እንደ ሔኖክ መልዕክት የሚተገበሩ ያድለን።

አለምፀሃይ ወዳጆ

ሄኖክ ያልኖረበትን ዘመን መርምሮ፣ ውስጠ ገመናችንን ፈልቅቆ ከእድሜው በላይ ተጨንቆ ይጠይቀናል፤ ራስን መናቅ፣ የራስን ሁሉ መጥላት እንደ ስልጣኔ ቆጥረን ከማንነታችን ስንሸሽ ሄኖክ በጥበቡ ኧረ ወዴት-ወዴት እያለ በራሳችን ቋንቋ በራሳችን ፊደል ይሞግተናል፤ ገዥዎቻችን እንደ ከብት ሊነዱን ሲያዙን፣ እኛም እንደ ከብት ለመነዳት ስናንኩበስ ሄኖክ ኧረ እምቢ እንበል ይለናል፤ በዚህ ዘመን በዚህ ትውልድ እንደ ሄኖክ ዓይነት እንቢ እንበል የሚል ወጣት ማግኘት ተስፋ ነው፤ ይህች የሄኖክ መፅሃፍ ድቅድቁን የጨለማ ዋሻ በብርሃን ለመተካት ፋኖሱን ለመለኮስ የተጫረች ክብሪት ናት።

ታማኝ በየነ

netsanet Publishing & Distribution Agency
www.npabooks.com